# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ተግባር አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# Contents


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የስጋት ስራ አመራር እና የኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ........ 2

የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ (Risk Management Policy &Strategy) ........ 2

የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ/Tax Audit Policy and Strategy/ ........ 3

ተቋማዊ ዳሰሳ ........ 3

የኢትዮጵያ ራዕይ ........ 3

የባለስልጣን መ/ቤቱ መቋቋም ........ 3

የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ ........ 3

የባለስልጣኑ ተልዕኮ ........ 3

የባለስልጣኑ ራዕይ ........ 4

የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ........ 4

የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ........ 4

የባለሥልጣን መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 5

የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 6

የኦዲቱ አላማ ........ 7

ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ ........ 7

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች ........ 7

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 10

ግኝቶች ........ 10

የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ሰነድ እንዲሁም የኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፣ ........ 10

የታክስ ኦዲት ተግባር ያስገኘውን ፋይዳ መገምገምን በተመለከተ፣ ........ 12

የግብር/ታክስ ኦዲት ስራዎች ዕቅድ እና አፈፃፀምን በተመለከተ፣ ........ 14

ኦዲቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን እና በኦዲት ዓይነቱ የተያዘ የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 16

ለኦዲት የሚመረጡት ግብር ከፋዮች ግልጽነት ባለው መንገድ እንዲመረጡ ማድረግን በተመለከተ፣ ........ 19

ሀ. የግብር ከፋይ ማህደራትን ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 19

ለ. ለታክስ ኦዲት የመምረጫ መስፈርቶች የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተጠናቅረው የሚያዙና የግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ የሚለይ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 21

ሐ. በየበጀት ዓመቱ ለኦዲት የተመረጡ ግብር ከፋዮች ዝርዝር መረጃን በማጠናቀር ለዋናው መ/ቤት እንዲተላለፍ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 23

ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 24
ከኦዲት ኬዝ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣ ........ 26
የሚከናወኑ ሁሉም ኦዲቶች ወጥነት ያላቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ለኦዲት ስራው አጋዥ የሆኑ ፎርማቶችን ማዘጋጀትን በተመለከተ፣ ........ 29
በቅድመ ኦዲት ዝግጅት የግብር ከፋዩን መብትና ግዴታ በግልጽ ማሳወቅን በተመለከተ፣ ........ 31
በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት የኦዲት መተማመኛ ስርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ........ 33
ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 35
በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣ ........ 38
የግብርናታክስ ቅሬታ አቀራረብና አፈታትን በተመለከተ፣ ........ 42
ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ማድረግ በተመለከተ፣ ........ 43
በኦዲት ውሳኔ መሰረት የሚገኙ ውዝፍ ዕዳዎችን ማስተዳደርን በተመለከተ፣ ........ 44
የኦዲት ጥራትን ከማስጠበቅ አንፃር የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ፣ ........ 46
**ክፍል ሦስት** ........ 50
***መደምደሚያ*** ........ 50
**ክፍል አራት** ........ 55
***የማሻሻያ ሃሳቦች*** ........ 55
**አባሪ 1 ፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር** ........ 59
አባሪ 2. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም ዘጠኝ ወራት የተከናወኑ የኦዲት ስራዎችና የተወሰነ ተጨማሪ ገቢ........ 60
አባሪ 3፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 61

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ሁሉም በዓለም ያሉ አገሮች ለልማት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለመሸፈን የታክስ ገቢን አንዱና ዋነኛ ምንጭ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህም አልፎ የአገር ዕድገትና ልማትን በአግባቡ ለመምራት የሚያገለግል ቁልፍ የፊሲካል ፖሊሲ መሣሪያ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የአንድ አገር መንግሥት ጥንካሬና ድክመት ትልቁ መለኪያም ይህንን ከታክስ የሚገኘውን ገቢ በብቃት ለመሰብሰብ በመቻልና ባለመቻል እንዲሁም የፊሲካል ፖሊሲውን በዕውቀትና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመተግበር እና ባለመተግበር ይወሰናል፡፡ በየትኛውም አገር መንግሥት መጠሪያና መልኩ የተለያየ ይሁን እንጂ እንደመንግሥት ለመቀጠልና የልማት ፖሊሲዎቹን ለማሳካት የሚያስፈልገውን ወጪ በታክስ ለመሸፈን በሚያደርገው ጥረትና ግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ ግብርን በፈቃደኝነት አምኖ ለመክፈል ባለመፈለግ መካከል ልዩነትና ክፍተት መኖሩ የተረጋገጠ ነው፡፡

2. ከላይ የተገለፀው የዓለም አገሮች እውነታ አገራችንንም በተጨባጭ የሚመለከት ሲሆን፣ መንግሥት ሥራውን እንዲሠራ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ገቢ ለማስገኘት፣ ብቃት ያለው ውጤታማ የፊሲካል ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር እና ፀረ-ጥገኝነት ትግላችንን ለማገዝ ሶስቱንም ዓላማዎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ለመፈፀም የመንግሥት ግብር አሰባሰብ ማሻሻያ ኘሮግራም ተነድፎ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፣ ሥራው በመቀጠል ላይም ይገኛል፡፡

3. መንግስት የምዕተ ዓመቱን የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ (MDG) ለማሳካት ዘርፈ ብዙ የሆኑ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ኢንዱስትሪ እንዲሁም ሰፋፊ የመሰረተ ልማት ስራዎች በተቀረፁት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አማካኝነት ተግባር ላይ ለማዋል ከፍተኛ የልማት ወጪ የሚጠይቀው በመሆኑ ይህንኑ ሊሸፍን የሚችል የሚታወቁ የገቢ ምንጮች (ብድር፣ ዕርዳታ እና የመንግስት ግምጃ ቤት) ቢኖሩትም አስተማማኝ እና ትክክለኛው ገቢ ከአገር ውስጥ የሚሰበሰበው ግብርና ታክስ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

4. ይኸ የገቢ ምንጭ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ከአገር ውስጥ የሚሰበሰበው ግብርና ታክስ ቢሆንም፣ በቀጣይ ዓመታት ከውጭ ንግድ የሚሰበሰበው ቀረጥ እየቀነሰ የአገር ውስጥ

የታክስ አሰባሰብ ድርሻ ከፍተኛውን የመንግስት ገቢ የሚሸፍን በመሆኑ የታክስ ባለስልጣኑ ከወዲሁ ተገንዝቦ በርካታ ስራዎችን መስራት ይጠበቅበታል፡፡

5. ከእነዚህ ስራዎች አንዱ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ የሚፈለግበትን ግብር በህጉ መሰረት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ እንዲከፍል ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የግብር ግዴታቸውን በማይወጡትና በሚያጭበረብሩት ላይ ስጋትን መሰረት ያደረገ የታክስ ኦዲት ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡

6. በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህንኑ በመረዳት የስጋት ምንጮችን በስርዓት በመለየት፣ የስጋት ደረጃውንና የኦዲት ፍላጎትን ለመወሰን የሚያስችል የስጋት ስራ አመራር እና የኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲቀረፅና ተግባር ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

## የስጋት ስራ አመራር እና የኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች

**የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ** (Risk Management Policy &Strategy)

7. ከግብርና ታክስ አንጻር ስጋት ማለት ባለስልጣን መ/ቤቱ የተቋቋመበትን አላማ እንዳያሳካ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ክስተቶች ማለት ነው፡፡ እነዚህ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በተቋሙ ተልዕኮዎች ማለትም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ቀረጥና ታክስ አሰባሰብ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ እና ሕገ-ወጥነት መከላከልና መቆጣጠር ላይ የራሱ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ ይህ ተፅዕኖ በስርዓት ለመምራትና በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ እንዲቻል የስጋት ምንጮች በስርዓት መለየት፣ ምንጮችን መሰረት በማድረግ መረጃ መሰብሰብ፣ በአግባቡ ማደራጀት፣ መተንተን፣ መመዘንና የመወሰን ሂደትን ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ ተቀርፆ ስራ ላይ ውሏል፡፡

8. የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ ዓላማ፤

- የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲ ዋና ዓላማ ሚዛኑን የጠበቀ የተቋሙ የቁጥጥርና/Control/ እና የድጋፍ/Facilitation/ ስርዓት እንዲኖር ማስቻል ሲሆን ጠቀሜታውም፡-
  - ✓ በሕጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ልማታዊ ባለሃብቶች ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት በመስጠት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ግብርና ታክስ የመክፈል ባህልን ለማሳደግ ይረዳል፤

- ✓ በወቅቱ ግብርና ታክስ የማያሳውቁ፣ ትክክለኛና የሚፈለግባቸውን ግብርና ታክስ የማይከፍሉ፣ እና የግብርና ታክስ ማጭበርበሮች ስራ ላይ በተሰማሩ ግብር ከፋዮች ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ያግዛል፡፡

**የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ**/Tax Audit Policy and Strategy/

9. የታክስ ኦዲት ፖሊሲ ዓላማ ታክስ ከፋዩ በራሱ እምነት ለታክስ አስተዳደሩ አሳውቆ የከፈለውን ግብርና ታክስ ካለው የታክስ ሕግ አንፃር የማጣራት ስራ ብቻ ሳይሆን የታክስ አስተዳደሩ አሰራር እንዲሻሻልና ግብር ከፋዩ በፈቃደኝነት እንዲከፍል ማስቻል ጭምር ነው፡፡

10. ስለሆነም የስጋት ስራ አመራር እና የኦዲት ዋና ዓላማ የስጋት ምንጮችን በመለየት፣ ስጋቶችን መመዘንና ቅደም ተከተል መስጠት(Risk Analysis) እና ስጋቶችን መሰረት በማድረግ ለግብር ከፋዮች የትምህርትና ምክር አገልግሎት መስጠትና ስጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት ዕቅድ ይዞ በዕቅዱ መሰረት እንደሁኔታው የዴስክ ኦዲት፣ ኢንቨስትጌሽን፣ ልዩ ኦዲት ወይም አጠቃላይ ኦዲት ማድረግ ነው፡፡

## ተቋማዊ ዳሰሳ

### የኢትዮጵያ ራዕይ

11. "በህዝቦች ተሳትፎና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን እውን ሆና ማየት ነው፡፡"

**የባለስልጣን መ/ቤቱ መቋቋም**

12. በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" ተብሎ እንዲቋቋምና ባለስልጣን መ/ቤቱም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡

**የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ**

**የባለስልጣኑ ተልዕኮ**

13. "ግብርን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል በማዳበር፣ ህግን ሊያስከብር የሚችል ሙያዊ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ በመጠቀም ዘመናዊ የታክስ እና የቀረጥ አስተዳደር

ስርዓት በመዘርጋት ለአገር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት በመሰብሰብ የዜጐችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ማረጋገጥ ነው፡፡”

**የባለስልጣኑ ራዕይ**

14. “በ2020 በአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ዘመናዊ እና ፍትሃዊ የታክስ አስተዳዳር ስርዓት ሰፍኖ አገራዊ ወጪ በአገራችን ገቢ ተሸፍኖ ማየት፡፡”

**የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓላማ**

15. የባለሥልጣኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ዘመናዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
- ኮንትሮባንድንና የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣
- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
- የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡

**የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

16. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል፡-

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡
- በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡
- ግብር/ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ግብር/ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፤ ተከፋይ የሚሆነውን የታክስ መጠን ይወስናል፤ ይሰበስባል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ በጥናትና ምርምሩ

ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፤ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**የባለሥልጣን መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል**

17. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋናው መ/ቤት እና የቅ/ጽ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር አጠናቆ ከጥቅምት/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ትግበራ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የባለስልጣን መ/ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ መረጃ (በአባሪ 1) ተያይዟል፡፡

18. ተቋሙ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን፣ የሚከተሉትን 5 የስራ ዘርፎች ማለትም፡- የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ስራዎች ዘርፍ፣ የቅርንጫፍ

ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ ፣ የህግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ፣ የኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ፣ የለውጥና ሞደርናይዜሽን ስራዎች ዘርፍ በምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚመሩና ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ ሆነው እንዲደራጅና እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ እንደዚሁም 23 ዳይሬክተሮች፣ 30 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ ሁለት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች፣ 153 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማክሮ ግብር ከፋዮች ወረዳዎች ጽ/ቤት እና ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የታክስ መሰብሰቢያ ማዕከላት በ22 መቅረጫ ጣቢያዎች እና በ50 መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በመያዝ ተደራጅቷል፡፡

19. በተመሣሣይ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤትን የሚመራ የጽ/ቤት ኃላፊ በዳይሬክተር ደረጃ የተዋቀረና የተደራጀ ሲሆን፣ በጽ/ቤቱም ሦስት የአማካሪዎች (የታክስና የጉምሩክ ጉዳዮች፣ የስትራቴጅክ ኢንተለጀንስ ጉዳዮች እና የኮሚዩኒኬሽንና የሰው ሃብት ልማት ጉዳዮች) የስራ መደብ እንዲሁም ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣ የስነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት፣ የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት እና የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት እንዲኖሩት ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡

20. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋናው መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሐምሌ 2005 ዓ.ም. 4,229 ወንድ 4,046 ሴት በድምሩ 8,275 ሠራተኞች የነበሩ ሲሆን፣ በመዋቅሩ መሰረት 7029 ክፍት የሥራ መደቦች ነበሩ፡፡

### የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

21. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃ እና ለካፒታል በጀት ከመንግስት በሚመደብለት በጀት እንዲሁም ከተለያዩ ለጋሽ አካላት ከሚገኘው እርዳታ ነው፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ገቢውን የሚሰበስበው ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ (ከወጪ እና ገቢ ንግድ ዕቃዎች)፣ ከሀገር ውስጥ ገቢ ግብር፣ ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የተጣራ ትርፍ እና ከኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ2003-2005 በጀት አመታት የተመደበለት በጀት፣ በስራ ላይ ያዋለው ሂሳብና በዚሁ በጀት ዓመታት የተያዘው የገቢ ዕቅድ እና የሰበሰበው ገቢ ከታች ባለው ሰንጠረዥ የተገለጸ ሲሆን፣ ከኮንትሮባንድ ዕቃ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ በዕቅድ የማይያዝና አፈጻጸሙም የማይታይ በመሆኑ በሰንጠረዡ ውስጥ አልተካተተም፡፡

| በጀት ዓመት | በጀት አጠቃቀም | | | በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበሰ ገቢ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ | የገቢ ዕቅድ በሚሊዮን | የተሰበሰበ ገቢ በሚሊዮን | በመቶኛ |
| 2003 | 595,614,423.97 | 564,163,943.98 | 94.71 | 54,178.53 | 50,816.45 | 93.79 |
| 2004 | 436,210,700.00 | 605,682,508.29 | 138.85 | 76,367.08 | 70,745.94 | 92.64 |
| 2005 | 541,522,700.00 | 730,369,871.71 | 134.87 | 101,658.83 | 84,414.41 | 83.04 |

## *የኦዲቱ አላማ*

22. *የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ባለስልጣን መ/ቤቱ በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባርን በመከላከል የገቢ ህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ብቃት ያለውና ውጤታማ የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት አሰራር መዘርጋቱን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ግድፈቶችን ለይቶ በማውጣት ግድፈቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡*

## **ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ**

23. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ **"በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነውን የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ተግባር አፈፃፀምን መገምገም"** የሚል ነው፡፡

## *የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች*

24. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit issues/ ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

- *የታክስ ህግ ተገዢነትን በማሳደግ ግብር ከፋዩ በፈቃደኝነት የታክስ ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባር/Tax audit function/ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤*
- *በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ያለው የታክስ ኦዲት አፈፃፀም ግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና ወጥነት ባለው መልኩ ደረጃውን ጠብቆ ስለመከናወኑ መገምገም፤*

*የሚሉት ናቸው፡፡*

25. *እነዚህንም የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ* 31 *የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች* (evaluative critera) *የተዘጋጁ ሲሆን፣ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይም ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጋር*


ውይይት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

26. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች ( Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2001 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 በጀት ዓመት እስከ 2005 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ስራ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ ኦዲት አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ሲሆን፣ በናሙና ከተመረጡት ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ ከምስራቅ እና ከምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ሲሆን፣ እንዲሁም በቅ/ጽ/ቤቶቹ በአካል በመገኘት የኦዲት ማስረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

## የአሰራር ሂደት መግለጫ (Process Description) የቀረጥና ታክስ ኦዲት ንዑስ የስራ ሂደት

6.4 ስእላዊ መግለጫ /አማራጭ ሁለት



# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ሰነድ እንዲሁም የኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፣

27. ባለስልጣኑ የተቋቋመበትን ዓላማዎች መሰረት ያደረገ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ፖሊሲና ስትራቴጂውንም ለማስፈፀም የሚያስችሉ ሰነዱን መሰረት ያደረጉ ማንዋሎች/መመሪያዎች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ አፈጻጸሙም በተቋም ደረጃ በየአመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡

28. ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚያከናውነውን የታክስ ኦዲት ብቃት ያለውና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባር በመከላከል የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፍል /Voluntary Compliance/ ማድረግን ዋና ዓላማ ያደረገ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረፅ በግንቦት 2002 ዓ.ም. እንዲፀድቅ አድርጓል፡፡

29. ይሁን እንጂ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂውን ባግባቡ ለማስፈፀም እንዲቻል ሰነዱን መሰረት ያደረጉ የአሰራር ማንዋሎች/መመሪያዎች/ ለማዘጋጀት እንዲሁም ከኦዲት ጋር ተያያዥ የሆኑ የተለያዩ ስልጠናዎች ለመስጠት ጠቅላላ ዋጋው ብር 2,670,439.42 የሆነና ዝግጅቱ በመጋቢት 2004 ዓ.ም. የሚጠናቀቅ የታክስ ኦዲት ማኔጅመንት እና ማንዋል ዝግጅት ፕሮጀክት በመስከረም 2004 ዓ.ም. የፀደቀ ቢሆንም፣ የታክስ ኦዲት አፈፃፀም መመሪያ/ማንዋል/፣ የታክስ ኦዲት ጋይድ ላይን፣ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር መመሪያ፣ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ጋይድ ላይን እንዲሁም የኢንቨስትጌሽን ኦዲት ማንዋሎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ተዘጋጅቶ እንዳልተጠናቀቀና ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. በተጨማሪም ቅ/ጽ/ቤቶችም በቀድሞ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በነበረበት ወቅት (በ1998 ዓ.ም.) በተዘጋጀ እና ወቅታዊ ባልተደረገ የኦዲት ማንዋሎች ከተለያዩ የግብር አዋጆችና ደንቦች ጋር በማያያዝ እየሰሩ እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት፣ የምዕራብ እና ምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

31. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ስራዎችን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር መመሪያዎች በየጊዜው የሚወጡና ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር መኖሩን፣ ለአብነትም ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ተቋማዊ የኦዲት ዕቅድ በማዘጋጀት ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲተገብሩት መደረጉን፣ ኦዲት አመራሩ ስራውን በብቃት ማስኬድ እንዲችል ሙያዊ ስልጠና መሰጠቱን፣ ኦዲት የሚደረጉ ማህደራትን መረጣ በተመለከተ የተዘረጋ አሰራር ስርዓት መኖሩን፣ ወጥ የሆነ የሪፖርት ማድረጊያ ፎርማት መዘጋጀቱን እንዲሁም የኦዲት ውሳኔ ማስታወቂያዎች በማን ተፈርሞ እንዲወጣ የሚያስችል መመሪያ መዘጋጀቱን ገልፀዋል፡፡

32. የኦዲት ማንዋሎች ዝግጅትን በተመለከተ ደግሞ ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ ማንዋሎች እንዲዘጋጁ ጥረት የተደረገ መሆኑንና ከዲ.ኤፍ.አይ.ዲ(DFID) በተገኘ የዕርዳታ ገንዘብ በ2004 በጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ የውጭ አማካሪዎችን በመለየት የኦዲት ማንዋሎች ተዘጋጅተው የነበሩ ቢሆንም፣ በተቋሙ እና በክልሎች የሚገኙ የኦዲት አመራሮች ግብዓት እንዲሰጡበት በተደረገበት ወቅት የተገኙት ግብዓቶች የኦዲት ማንዋሎቹ ባሉበት ደረጃ የሚያሰሩና በስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በቀላሉ ለመፍታት የሚያግዙ አለመሆናቸው በመገለፁ በድጋሚ ታይቶ እንደገና እንዲሰራ በመወሰኑ በአሁኑ ወቅት በተቋሙ ባለሙያዎች በራስ አቅም ለማጠናቀቅ በተወሰደ እርምጃ የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ማንዋል ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን፣ የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ማንዋል ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ የመጀመሪያው ረቂቅ ወጥቶ የተቋሙ ባለሙያዎች ግብዓት እንዲሰጡበት በማድረግ 85 በመቶ ግብዓት ተሰብስቦ በግብዓቱ መሰረት ማስተካከያ በመደረግ ላይ መሆኑን፣ እንዲሁም ጎን ለጎን የስልጠና ሞጁል እየተዘጋጀ ከመሆኑ በተጨማሪ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ማንዋል ዝግጅቱ 50 በመቶ የተጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

33. በመሆኑም ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው በውጭ አማካሪዎች የተዘጋጁት ማንዋሎች ባሉበት ደረጃ የማያሰሩ በመሆናቸውና ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን እና ባለስልጣን መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በዝግጅት ላይ የሚገኙት ማንዋሎች በአፋጣኝ ተጠናቀው ወደ ተግባር እንዲገቡ ባለመደረጉ በቅ/ጽ/ቤቶች ያለው የታክስ ኦዲት የአሠራር ሥርዓት ወጥ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዳይይከናወን አድርጓል፡፡

**የታክስ ኦዲት ተግባር ያስገኘውን ፋይዳ መገምገምን በተመለከተ፣**

34. የታክስ ኦዲት ያስገኘውን አስተዋፅኦ ከሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት በመለየት ሊለካ በሚችል መልኩ ለማቀድ፣ አፈፃፀሙንም ለመገምገምና ለማሻሻል የሚያስችል የታክስ ኦዲት መርህን/ tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት ሊዘጋጅና እያንዳንዱ የኦዲት ስራ እንዲሁም አጠቃላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የኦዲት ተግባር ሊገመገም ወይም ሊመዘን ይገባል፡፡

35. በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባርን በመከላከል የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፍል ለማድረግ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ የታክስ ኦዲት ነው፡፡

36. በዚህ መሰረትም በባለስልጣን መ/ቤቱ አገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን መነሻ በማድረግ በተዘጋጀው የ2003-2007 በጀት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ በዕቅድ ዘመኑ ተግባራዊ ከሚያደርጋቸው ግቦች እና ስትራቴጂክ እርምጃዎች መካከል በፈቃደኝነት የሚከፈለውን የገቢ ድርሻ በየዓመቱ በ7% እንደሚያድግ እና ሕገ-ወጥ ንግድና ታክስ ማጭበርበርን በተመለከተ ደግሞ በየዓመቱ በ10% እንደሚቀንስ ታቅዷል፡፡

37. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጁት የ2004 እና የ2005 በጀት ዓመታት ተቋማዊ የታክስ ኦዲት ዕቅድ ሰነዶች በተከለሱበት ወቅት እንደ ተቋም በየበጀት ዓመታቱ ከተያዘ የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ዕቅድ ግብ ውስጥ የኦዲት ውጤታማነት መለኪያዎች ተብለው የተቀመጡት፡- ተቋሙ በየግብር ዘመኑ እደርስበታለሁ ብሎ በውጤት ተኮር ዕቅድ የያዘውን የገንዘብ መጠን ግብ ለማሳካት በኦዲት የሚገኝ ተጨማሪ ግብር/ታክስ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ማድረስ፣ በአንድ ኦዲተር የሚገኘውን ተጨማሪ ግብር/ታክስ ማሳደግ፣ ከአንድ ማህደር የሚገኘውን ተጨማሪ ግብር/ታክስ እንዲያድግ አድርጎ መፈፀም እና በኦዲት የተገኙ ተጨማሪ ግብርና ታክስ ሙሉ በሙሉ እንዲሰበሰቡ ማድረግ የሚሉት ብቻ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባርን የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ

ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፈል ከማድረግ አንፃር በዕቅድ ዘመኑ ከተቀመጡት ዒላማዎች(Targets) እና የአፈጻጸም መለኪያዎች አንፃር እንደማይታቀድና ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት/ፋይዳ እንደማይገመገም በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

39. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተቋም ደረጃ ከተዘጋጀው ሚዛናዊ ስኮር ካርድን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን ተቋማዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ (2003-2007) በመነሳት ቅ/ጽ/ቤቶች የራሳቸውን ዕቅድ ካስኬድ በማድረግ የየበጀት ዓመታቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀመጠውን ዓላማዎች ማለትም የኦዲት ሽፋንን ማሳደግ፣ በኦዲት የሚገኘውን ተጨማሪ ገቢ በቅ/ጽ/ቤቶች የገቢ ዕቅድ የሚኖረውን ድርሻ በመቶኛ፣ የስጋት ስራ አመራር ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ የግብር ከፋይ ማህበረሰብ የህግ ተገዥነትን ከፍ ለማድረግ የሚከናወን ስራ የሚገኝበት መኖሩን እና ከዚህም ጋር በተያያዘ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን በስጋት የመምረጥ ስራ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ መደረጉን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በአፈፃፀም ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊነቱን የመገምገሙና የማስተካከሉ ሁኔታ ሊለያይ ስለሚችል በቀጣይ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ተደራሽ መሆኑን ለመከታተል የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ከባድ የቤት ስራ እንደሚጠብቀው የሚያምኑ መሆኑንና በታክስ ኦዲት ፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት በቀጣይ እንደተቋም መስራት የሚገባቸው መሆኑን እንደሚቀበሉት ገልፀዋል፡፡

40. በመሆኑም የተከናወኑ የታክስ ኦዲቶች በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባር በመከላከል የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፍል ያደረገውን አስተዋፅኦ መገምገም የሚያስችል የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በባለስልጣን መ/ቤቱ ህግ ማስከበርን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዘመኑ የያዛቸውን ዒላማዎች ከማሳካት አንፃር የታክስ ኦዲቱ ያበረከተው ተጨባጭ አስተዋፅኦ ወይም ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት ወይም ፋይዳ ለማወቅና ለመመዘን አላስቻለም፡፡

**የግብር/ታክስ ኦዲት ስራዎች ዕቅድ እና አፈፃፀምን በተመለከተ፣**

41. በታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂው ላይ የተቀመጠውን የታክስ ኦዲት መርህ /tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የረዥም፣ መካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ተቋማዊ ዕቅድ ሊዘጋጅ እና ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ሊደረግ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ ሊያዘጋጁና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የዕቅድ አፈጻጸሙም በየወቅቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ በግምገማው ውጤት መሰረትም ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

42. በኦዲቱ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂውን መሰረት ያደረገ አንድ ወጥ ተቋማዊ ዕቅድ አሳታፊ በሆነ መንገድ አዘጋጅቶ ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ የተደረገ ቢሆንም፣ ቅ/ጽ/ቤቶች የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃ በተከለሰበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት በተቋም ደረጃ የተቀመጠው ዕቅድ ከ848 ግብር ከፋዮች ውስጥ 544(64%) ማህደራትን አጠቃላይ ኦዲት፣ ልዩ ኦዲት እና ውስን ኦዲት ማድረግ ሲሆን፣ ነገር ግን በቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት ዕቅድ ላይ 213 አጠቃላይ ኦዲት ብቻ ታቅዶ 190(22%) ብቻ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በቅ/ጽ/ቤቱ የህግ ማስከበር እና የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደቶች እንደየቅደም ተከተላቸው 2 ልዩ ኦዲት እና 158 የዴስክ ኦዲት የተከናወነ ሲሆን፣ በጠቅላላው በበጀት ዓመቱ የ350 ግብር ከፋይ ማህደራት ኦዲት ተከናውኗል፡፡ ይህም በቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኙት ግብር ከፋዮች ውስጥ 41% ብቻ የሸፈነ መሆኑን፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ በተቋም ደረጃ በቅ/ጽ/ቤቱ ከሚገኙ 864 ግብር ከፋዮች ውስጥ የ835(97%) ማህደራትን በአጠቃላይ ኦዲት፣ ልዩ ኦዲት እና ውስን ኦዲት ለማድረግ ቢሆንም፣ በቅ/ጽ/ቤቱ ዕቅድ ላይ ግን 170 አጠቃላይ ኦዲት፣ 10 ልዩ ኦዲት እና 480 የዴስክ ኦዲት በድምሩ 660 የግብር ከፋይ ማህደራትን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ 149 አጠቃላይ ኦዲት፣ 5 ልዩ ኦዲት እና

331 የዴስክ ኦዲት በድምሩ 485 የግብር ከፋይ ማህደራት ማለትም 56 በመቶውን ብቻ ኦዲት ያከናወነ መሆኑን፣

- ✓ ኦዲት የሚደረገውን የግብር ዘመን በተመለከተ ደግሞ የዋናው መ/ቤት ዕቅድ መሰረት ያደረገው የአንድ ግብር ከፋይ ኦዲት የሁለት ግብር ዘመንን ቢሆንም፣ በቅ/ጽ/ቤቱ ዕቅድ የአራት ግብር ዘመንን በሁለት ኦዲተር ኦዲት ለማድረግ የታቀደና አፈጻጸሙ ግን እስከ ስድስት የግብር ዘመን እንደሚሸፍን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡

43. ስለጉዳዩ የቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤት በየግብር ዘመኑ በሚታቀደው በየኦዲቱ አይነት የተያዘው ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮች ብዛት መለያየትን በተመለከተ በዋናው መ/ቤት የተዘጋጀው በአንድ ኦዲተር እንዲሰራ መነሻ ያደረገ እና በቀን 8 ሰዓት ሙሉ ጊዜ በኦዲት ስራ ላይ ኦዲተሮች እንደሚሰሩ ታሳቢ ያደረገ ቢሆንም፣ በተግባር የሚያጋጥሙ በተለይ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች በገቢ መጠን እና በንግድ ዘርፍ የተለዩ እና በአዲስ አበባ በሁሉም ክፍለ ከተማ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ ወረዳ ከተሞች በተለይ የማምረቻ ተቋሞች/ከአቃቂ እስከ ዱከም፣ አለምገና፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ../ ቦታዎች ላይ ኦዲተሮች በሕዝብ ትራንስፖርት ተጠቅመው እስኪደርሱ እንዲሁም አልፎ አልፎ ከዋናው መንገድ ገባ ያሉ የማምረቻ ተቋሞች ለመድረስ የሚወስደውን ጊዜ ከዕቅዱ ልዩነት ዋናው ተጠቃሽ ከመሆኑ በተጨማሪ በዋናነት ኦዲት ተደርገው ከአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴና በግብር ይግባኝ፣ የሚታዩ ጉዳዮች ላይ ቀርቦ ማስረዳት፣ መተሳሰብ ካለው ተሳስቦ መቅረብ እና በአቤቱታ አጣሪና በግብር ይግባኝ ውሳኔ መሰረት የማስተካከያ የኦዲት ስራ የሚወስደውን ጊዜ የዋናው መ/ቤት ዕቅድ ያላካተታቸው በመሆኑ የዕቅድ ልዩነት ማጋጠሙን ገልፀዋል፡፡

44. ኦዲት የሚደረገውን የግብር ዘመን መለያየትን በተመለከተ ደግሞ በተመላሽ ጥያቄ ኦዲት የሚደረጉ ከሆነ ተመላሽ ከጠየቀበት ግብር ዘመናት በፊት ያሉት ግብር ዘመናት ኦዲት እንደሚደረጉ ምክንያቱም ተመላሽ የሚሰጠው ሌላ የግብርና ታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑ ተረጋግጦ በመሆኑ፣ በተጨማሪም ከቅ/ጽ/ቤቱ የህግ ማስከበር የስራ ሂደት መረጃ(ጥቆማ) መሰረት የሚቀርብ የኦዲት ጥያቄ፣ ከዋናው መ/ቤት የኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ጥናት የተደረገባቸው እና ኦዲት እንዲደረጉ የሚጠየቁ/ ለተከታታይ ግብር ዘመናት ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች/ የሁሉም ግብር ዘመን ኦዲት

*ማድረግ ስለሚጠይቅ እስከ ስድስት ግብር ዘመን የሚደርስ ኦዲት የሚካሄድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡*

45. *ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቅ/ጽ/ቤቶች ከሚያጋጥማቸው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለአንድ ግብር ከፋይ የተለያየ ግብር ዘመንን ኦዲት ሊያደርጉ እንደሚችሉ፣ ነገር ግን በዋናው መ/ቤት ተዘጋጅቶ የወረደው የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እንዲሁም በየዓመታቱ የሚታቀደው ተቋማዊ ዕቅድ አንድን ግብር ከፋይ ለዚህን ያህል ዓመት ኦዲት ስታደርጉ ነው ስታንደርድ ቀኑ የሚይዘው ብሎ ያስቀመጠው ነገር አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት የዕቅድ ሰነዱ ሲከለስ የዕቅድ ዝግጅቱ የሚመለከታቸውን ቅ/ጽ/ቤቶች ያሳተፈ እንደሆነ የተገለፀ ከመሆኑ አንፃር በዕቅድ ዝግጅት ወቅት የተጠቀሱት ጉዳዮች ግንዛቤ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ የኦዲት ቡድኑ የሚያምን በመሆኑ፣ በተጨማሪም በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሰረት አንድ የመንግስት ሰራተኛ በቀን ለ8 ሰዓት የመስራት ግዴታ እንዳለበት የተደነገገ ከመሆኑ አንፃር የተሰጠውን ምላሽ እንደ ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡*

46. *በመሆኑም ቅ/ጽ/ቤቶች እንደ አንድ ተቋም የተዘጋጀውን ወጥ የሆነ የኦዲት ዕቅድ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅተው ተግባራዊ አለማድረጋቸው በተቋሙ የተያዘውን የኦዲት ሽፋን ግብ ማሳካት እና በተሰማራው ውስን የሰለጠነ የኦዲት ሙያተኛ ልክ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት አላስቻለም፡፡ በተጨማሪም ኦዲት የሚደረገውን የግብር ዘመንን ያላገናዘበ የኦዲት የጊዜ ተመን በመኖሩ የሚከናወነው ኦዲት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡*

***ኦዲቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን እና በኦዲት ዓይነቱ የተያዘ የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ፣***

47. *የግብር ከፋዮች ደረጃን፣ የኦዲት አይነት እንዲሁም የንግዱን እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ የኦዲት የጊዜ ተመን/ ስታንደርድ/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለኦዲት የተመሩ የግብር ከፋይ ማህደራት/ፋይሎች/ ኦዲት በተቀመጠው የጊዜ ዕቅድ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ኦዲትም በተቀመጠው የኦዲት ጊዜ ተመን ውስጥ ስለመከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡*

48. *በኦዲቱ ወቅት በለስልጣን መ/ቤቱ ለእያንዳንዱ የኦዲት አይነት እንዲሁም በየቅ/ጽ/ቤቶች የሚገኙ ግብር ከፋዮችን ደረጃ በመለየት ስታንደርድ ማዘጋጀቱ*

ታውቋል፡፡ በዚህ መሰረት ከታች በሠንጠረዡ በተገለጸው መልኩ በተቋም ደረጃ በተዘጋጁት የኦዲት ዕቅዶች ላይ ለእያንዳንዱ ኦዲት የተሰጠ የጊዜ ሰሌዳ ተቀምጧል፡፡

**ለየኦዲት ዓይነት የተሰጠ የሰዓት ክፍፍል በቀን**

| የኦዲት ዓይነት | ለእያንዳንዱ ኦዲት የተሰጠ የጊዜ ሰሌዳ (በቀናት) | | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በ2004 በጀት ዓመት | | | ለ2005 ስምምነት የተደረሰበት | | | |
| | ከፍተኛ ግብር ከፋዮች | መካከለኛ ግብር ከፋዮች | አነስተኛ ግብር ከፋዮች | ከፍተኛ ግብር ከፋዮች | መካከለኛ ግብር ከፋዮች | አነስተኛ ግብር ከፋዮች | |
| አጠቃላይ ኦዲት | 31 | 22 | | 30 | 22 | 3 | |
| ልዩ ኦዲት | 41 | 30 | | 40 | 30 | 30 | |
| ውስን ኦዲት | 4 | 4 | | 4 | 4 | 4 | |
| ዴስክ ኦዲት | 10 | 10 | | - | - | - | በግብር አወሳሰን፣ አሰባሰብና ክትትል በኩል ይሠራል ተብሎ ስለተያዘ በዚህ ላይ መግለጽ አላስፈለገም፡፡ |

49. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የምዕራብና የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች እያንዳንዱ የተጠናቀቀ ኦዲት የወሰደው ጊዜ፣ የተከናወነው የኦዲት አይነት እና ሌሎች ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ ተጠናቅሮ በስራ ሂደቱ እንዲያዝ የሚደረግ ስለመሆኑ እና የኦዲት ቡድን አስተባባሪውም ሆነ የስራ ሂደቱ እያንደንዱ ኦዲቶች በታቀደላቸው ወቅት እና የጊዜ ተመን እየተከናወኑ ስለመሆኑ በየወቅቱ ክትትል በማድረግ አፈፃፀማቸውንም በመገምገም ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ ስለመሆኑ ማስረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

50. ነገር ግን በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከቀረቡት መረጃዎች እና በናሙና ከታዩት የግብር ከፋይ የኦዲት ፋይሎች ኦዲቱን ለመጀመር የሚፃፈውን የደብዳቤ ቀን እና የኦዲት ውሳኔው የመጣበትን ቀን በማነፃፀር ለመረዳት እንደተቻለው በቅ/ጽ/ቤቱ ከተከናወኑ ኦዲቶች ውስጥ አንዳንድ አጠቃላይ ኦዲቶች በዕቅድ ከተያዘው ጊዜ በላይ ከ34-358 ቀናት የወሰዱ መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ የቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የታክስ ኦዲት ስራ ሂደት የየወሩ ዕቅድ ክንውን ሲገመግም አብሮ እያንዳንዱ ኦዲት የወሰደውን ጊዜ እና በወር ውስጥ ኦዲት ተደርገው ውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸውን ግብር ከፋዮች ብዛት በአማካኝ የወሰደው ጊዜ ላይ በተለይ ረጅም ጊዜ የወሰዱ የኦዲት ስራዎች ከምን አኳያ እንደሆነ ከቡድን አስተባባሪዎች ጋር የሚገመገም መሆኑን፣ በዚህም መሰረት አንድ

የግብር ከፋይ ኦዲት የወሰደው በአማካኝ በ2004 በጀት ዓመት 29.68 ቀናት እና በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ 37.2 ቀናት መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ ይሁን እንጂ የኦዲት ስራቸው ረጅም የስራ ጊዜ የሚወስዱ ድርጅቶች ወይም የንግድ ዘርፎች/ አንድ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሆነው የተለያዩ ፕሮጀክቶች የያዙ ድርጅቶች/ የሚገኙ መሆኑንና ኦዲት የሚደረጉት በተጀመረበትና በተጠናቀቀበት ቀን መካከል ባለው ጊዜ ሳይሆን ኦዲተሮች በመሃል ማስረጃዎች እስከሚሟሉላቸው ሌሎች ድርጅቶችን ኦዲት እንደሚያደርጉ እንዲሁም በመሃል ቀደም ብለው የሰሩት የኦዲት ስራ ላይ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴና በግብር ይግባኝ ውሳኔ መሰረት የማስተካከያ የኦዲት ስራዎችን የሚሰሩ መሆኑን፣ በዚህ መሰረትም በየወሩ በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት ከሚቀርቡ ሪፖርቶች ከፍተኛውን ጊዜ የወሰደው የኦዲት ስራ የተሰራበት ጊዜ ብቻ ተቆጥሮ ስድስት ወራት የፈጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኦዲቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን እየተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ የታክስ ኦዲቱ እያንዳንዱ የኦዲት ስራ የወሰደውን ጊዜ በአግባቡ ተሰልቶ በየወሩ እንዲላክ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተቀርፆ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው የተደረገ ቢሆንም፣ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ይህንን መሰረት ያደረገ ሪፖርት እንደማይልኩ፣ እንዳጋጣሚ ሆኖ የኦዲቱ ናሙና ያረፈባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ይህንኑ ሪፖርት ሞልተው እንደማይልኩ በዳይሬክቶሬቱ በኩል የታየና ማስተካከያ እንዲያደርጉ የተገለፀላቸው መሆኑን እና በቀጣይ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ተቋማዊ ዕቅዱ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ በመሆኑ፣ የተቀመጠው ስታንደርድ ሰዓት/ቀን/ ወይም ኦዲቱ የሚሸፍነው የግብር ዘመን ይህን ነው በሚል በዋና መ/ቤት ደረጃ የተገለፀ ማስረጃ አለማግኘታቸውን ገልፀዋል፡፡

53. በመሆኑም በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የግብር ከፋዮችን እርካታ መፍጠር ካለማስቻሉ በተጨማሪ በቅ/ፅ/ቤቶች ከሚገኘው ግብር ከፋይ ብዛትና በተቋሙ ካለው ውስን የኦዲት ባለሙያ አንፃር በቂ የኦዲት ሽፋን ባለመኖሩ በኦዲት ሊገኝ የሚችል ተጨማሪ ገቢ ሳይሰበሰብ የይርጋው ጊዜ እንዲያልፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ለኦዲት የሚመረጡት ግብር ከፋዮች ግልጽነት ባለው መንገድ እንዲመረጡ ማድረግን በተመለከተ፣**

**ሀ. የግብር ከፋይ ማህደራትን ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

54. የግብርና ታክስ ኦዲት ስራዎችን ተገቢና ምቹ በሆነ መልክ ለማደራጀት፣ ለመመደብና ለመገምገም እንዲሁም ግብር ከፋዩን በእኩልነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የአሰራር ስርዓት በአግባቡና ወጥ በሆነ መልኩ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ስለመደረጉ በዋና መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡

55. በኦዲቱ ወቅት ግብር ከፋዮች ለኦዲት የሚመረጡበት ሂደት የታክስ ኦዲትና የስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት ያደረገ እንዲሆን በደብዳቤ ቁጥር 1-0/7/1 ሐምሌ 8 ቀን 2002 ዓ.ም. ከዋናው ዳይሬክተር መመሪያ የተላለፈና መመሪያውም የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ የስጋት ደረጃ ለመለየት የሚያስችሉ አራት የስጋት መመዘኛ መስፈርቶችን ያካተተ መሆኑን፣ በተጨማሪም በየቅ/ጽ/ቤቱ በቅ/ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ቢያንስ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር ማህደራት እንደ ስጋት ደረጃቸው መመረጥ እንዳለባቸው የተገለፀ መሆኑ ታውቋል፡፡

56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት እያከናወኑ ስለመሆኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት፣ ከግብር አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት፣ ከሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት እና ከቅ/ጽ/ቤቱ የሕግ ተገዢነት ቡድን የተውጣጣ መራጭ ኮሚቴ የተቋቋመ እንደሆነና በመመሪያው መሰረት ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ ኮሚቴው የግብር ከፋይ ማህደራትን በመምረጥ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

57. የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ በቁጥር ምዕ/3.1.0/004/8348 በ08/5/04 ዓ.ም. ከተለያዩ ክፍሎች 5 ሰዎች ተመድበው 16ቱን የመምረጫ መስፈርቶች በመጠቀም በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የሚደረጉ ማህደራትን በማንዋል መርጠው ለኦዲት አስተላልፈው ኦዲት የተደረገ ቢሆንም፣

በ2005 በጀት ዓመት የግብር ከፋይ መረጃ የማጥራት ስራ ተጠናክሮ ተሰርቶ በሲግታስ መምረጫ መሰረት በሲስተም ብቻ እንዲሰራ በመባሉ ከዚህ ወቅት ጀምሮ ኮሚቴ የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን በቅርብ ከዋናው መ/ቤቱ በቁጥር 3.4.0/197/7 በ04/02/06 በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት ኮሚቴው በቅ/ጽ/ቤቱ በድጋሚ በመቋቋም ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

58. የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግን በተለያዩ ስብሰባዎች እና በጥናት ሰነዶች ላይ የኪራይ ሰብሳቢነት መገለጫ ተብለው ከተለዩት አንዱ በየቅ/ጽ/ቤቶች የሚቋቋመው ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን የሚመርጠው ኮሚቴ ነው በመባሉ ምክንያት ቅ/ጽ/ቤቱ የመራጭ ኮሚቴውን ሊያቋቋም አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

59. በተቋቋመው አካል የሚከናወነውን የግብር ከፋይ ማህደራትን ለታክስ ኦዲት የመምረጥ ሂደት ለመምራት የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የመራጭ ኮሚቴውን ተግባርና ሃላፊነት በተመለከተ ቅ/ጽ/ቤቱ፣ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና በስጋት ስራ አመራር መሰረት የ2003 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም እና በቀጣይ መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ባዘጋጀው የግምገማ ሰነድ ላይ ያስቀመጠ መሆኑን የገለፁ ሲሆን፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ግን ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን ለመምረጥ የተቋቋመ ኮሚቴ ባለመኖሩ ኮሚቴው የሚሰራበት የአሰራር መመሪያ አለመዘጋጀቱ ተገልፀዋል፡፡

60. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በየቅ/ጽ/ቤቱ የመራጭ ቡድን በቅ/ጽ/ቤት ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚመራ ቢያንስ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር ማህደራት እንደ ስጋት ደረጃቸው መመረጥ እንዳለባቸው በዕቅድ ላይ የተገለፀ ከመሆኑ ባሻገር በ2006 በጀት ዓመት ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርጉ በድጋሚ የማሳሳብ ስራ እንደተሰራ፣ ሆኖም ይህ ሁኔታ እየተሰራበት ስለመሆኑ የሚደረገው ክትትል ላይ ውስንነቶች እንዳለባቸው የሚያምኑና በቀጣይ የሚያስተካክሉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

61. በመሆኑም በቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት እንዲደረጉ የተወሰኑ ማህደራት/ኦዲት ኬዝ/ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው እንዲሁም ወጥ በሆነ መልኩ የተመረጡ እንዲሆን ለማድረግ አላስቻለም፡፡

### ለ. ለታክስ ኦዲት የመምረጫ መስፈርቶች የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተጠናቅረው የሚያዙና የግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ የሚለይ መሆኑን በተመለከተ፣

62. የግብር ከፋዮች መረጃ (profile) እንዲሁም በታክስ ኦዲትና ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂው መሰረት ለታክስ ኦዲት የመምረጫ መስፈርቶች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሰባሰብ አጠናቅሮ በመያዝ የስጋት መምረጫ መስፈርቶቹን አቀናጅቶና አዋህዶ ጥቅም ላይ በማዋል የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ስጋት ደረጃ በማለት በግልጽ በማስቀመጥ በየበጀት ዓመቱ ደረጃ እንዲይዙ ሊደረግ እና በየበጀት ዓመቱ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮች ሊመረጡ ይገባል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የመራጭ ኮሚቴው በታክስ ኦዲት ስጋት ስራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ መሠረት የሥራ ሂደቱ መረጃዎችን ከSIGTAS፣ ከዋናው መ/ቤት የኢንተለጀንስ የታክስ መረጃ እና የሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት የከፍተኛ ግብር ከፋዮችን መረጃ በማጠናቀር እና መረጃውን በመተንተን በስጋት ደረጃ የመለየት ሥራዎችን እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

64. የምስራቅ እና ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በቅ/ጽ/ቤቶቹ የመራጭ ኮሚቴ ያልተቋቋመ በመሆኑ መረጃዎች በኮሚቴው ተደራጅተው የተቀመጡበት ሁኔታ አለመኖሩን እና ቀደም ሲል ኦዲት የሚደረጉ ማህደራት በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት የሚከናወን መሆኑን፣ ነገር ግን በ2005 በጀት ዓመት የግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ለመወሰን እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው በመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት በተለዩት እና በተላኩት የመረጃ ማስተካከያ ነጥቦች ላይ ሙሉ በሙሉ የመረጃ ማጥራት ስራ ተሰርቶ መጠናቀቁን ገልፀዋል፡፡

65. ይሁን እንጂ በቅ/ጽ/ቤቶቹ የቀረቡ መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

66. በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት፤

- በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲደረጉ የመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸው እና በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት አስተያየት ተሰጥቶባቸው ለየኦዲት ቡድኑ የተደለደሉ የ206 ግብር ከፋዮች ዝርዝር ቢኖርም፣ ከግብር ከፋዮቹ ስም ዝርዝር እና

የግብር ከፋይ መለያ ውጭ የተሰጣቸው የስጋት ደረጃ አለመጠቀሱ፣ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት 190 ግብር ከፋዮች ውስጥ በስጋት መስፈርት መሰረት የተመረጡት 100 ግብር ከፋዮች ብቻ መሆናቸውንና ቀሪዎቹ 90 ግብር ከፋዮች ግን በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲደረጉ የመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸው እና በቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት አስተያየት ተሰጥቶባቸው ለየኦዲት ቡድኑ ከተደለደሉት የ206 ግብር ከፋዮች ዝርዝር ውስጥ ያልተገኙ መሆኑ፣

- በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ በበጀት ዓመቱ ኦዲት እንዲደረጉ የተመረጡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ፣ ሲግታስ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን በስጋት መስፈርት መሰረት የሚመርጥበት ሞጁል ከነሐሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ በመስራቱ በቅ/ጽ/ቤቱ ከተመዘገቡት 864 ግብር ከፋዮች ውስጥ የ718 (83 በመቶ) ግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ተሰጥቷቸው የወጡ መሆኑንና ሲስተሙ የስጋት ደረጃ ውጤት ከሰጣቸው 718 ግብር ከፋዮች ውስጥ 75 የመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋሞች በኦዲት የማይካተቱ እና 50 ግብር ከፋዮች ቀደም ሲል ኦዲት የተደረጉ ተቀንሶ ቀሪዎቹ 593 ግብር ከፋዮች በሶስቱም የኦዲት አይነቶች ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ መሆኑን፣ በተጨማሪም የሲግታስ የስጋት ደረጃ ካልተሰጣቸው 146 ግብር ከፋዮች ውስጥ 67 ግብር ከፋዮች በዕቅድ ተካተው አጠቃላይ 660 ግብር ከፋዮች ለኦዲት የተመረጡ መሆኑን፣
- ነገር ግን ለ2006 የበጀት ዓመት ለኦዲት የተመረጡ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ በስጋት መስፈርት መሰረት ለመምረጥ ተሞክሮ የሲግታስ ውስንነት በመኖሩ በቅ/ጽ/ቤቱ ካሉት አጠቃላይ 991 ግብር ከፋዮች ውስጥ የስጋት ደረጃ የወጣላቸው የ254 ግብር ከፋዮችን ብቻ ሲሆን፣ የቀሩት 737 ግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ግን ማየት አለመቻሉ ታውቋል፡፡

67. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ከመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ለቅ/ጽ/ቤቱ ከተላኩት ግብር ከፋዮች ውስጥ ብዛታቸው 325 ድርጅቶች ታክስ ማዕከላቸው ምዕ/አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ነው ከሚለው በስተቀር በትክክል ስለመሆናቸው ያልተጣራ እና ከተላኩት የቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከፋዮች

ዝርዝር ውጪ የሆኑ እና በመረጃ ማጥራቱ ስራ ያልተካተቱ ብዛታቸው 2028 የሆኑ ግብር ከፋዮች ስለመኖራቸው ታውቋል፡፡

68. በተጨማሪም ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ከመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተላለፈው መመሪያ መሰረት መረጃ የማጥራት ስራዎቹ በሶስት ክፍሎች የሚከፈሉ ሲሆን፣ እነርሱም፡- ከግብር ከፋዮች አጠቃላይ መረጃ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የማጥራት ስራ፣ ከግብር ከፋዮች የተፈፀመላቸው የግብር/ታክስ ተመላሽ ምዝገባ ስራ እና ከግብር ከፋዮች የኦዲት ታሪክ (ኦዲት ኬዝ) ጋር በተያያዘ የመረጃ ምዝገባ ስራዎች የተገለፁ ቢሆኑም፣ ከተገለፁት ሶስቱ የመረጃ ማጥራት ክፍሎች ውስጥ የግብር ከፋዮች አጠቃላይ የምዝገባ መረጃ ጋር የተያያዘውን ስራ ብቻ መሰራቱ ታውቋል፡፡

69. ስለጉዳዩ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን ሐምሌ/2003 ለመምረጥ የሲግታስ የስጋት መምረጫ ሞጁሉ ሊሰራ ባለመቻሉና በማንዋል የሲግታስ መምረጫ መስፈርት መሰረት አጠናቆ የሂሳብ ስሌቱን ማስቀመጥ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የተመረጡትን የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ የስጋት ደረጃ ለማስቀመጥ አለመቻላቸውን፣ በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲደረጉ የመራጭ ኮሚቴው የመረጣቸውና ለየኦዲት ቡድኑ ከተደለደሉት ግብር ከፋዮች ዝርዝር ውስጥ ያልተገኙትን በተመለከተ ደግሞ በ2003 በጀት ዓመት በስጋት መስፈርት ተመርጠው ኦዲት ሳይደረጉ ለቀጣዩ ግብር ዘመን የዞሩና ኦዲታቸው የተከናወነና በበጀት ዓመቱ ከደንበኞች በቀረበ የአገልግሎት ጥያቄ መሰረት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚያካትት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. በመሆኑም በቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሚገኙ ለሁሉም ግብር ከፋዮች የጠራና የተደራጀ መረጃ (profile) ባለመያዙ የስጋት መምረጫ መስፈርቶቹን አቀናጅቶና አዋህዶ ጥቅም ላይ በማዋል የሁሉንም የሚያስተዳድሯቸውን ግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ በግልጽ እንዲታወቅና ለኦዲት የተመረጡት ግብር ከፋዮችም ግልጽነት ባለው መንገድ ስለመመረጣቸው ለማረጋገጥ አላስቻለም፡፡

### ሐ. በየበጀት ዓመቱ ለኦዲት የተመረጡ ግብር ከፋዮች ዝርዝር መረጃን በማጠናቀር ለዋናው መ/ቤት እንዲተላለፍ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣

71. ቅ/ጽ/ቤቶች በየበጀት ዓመቱ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን በመለየትና ለቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ሪፖርት በማቅረብ፣ ከቅ/ጽ/ቤቱ የሚሰጡ ግብዓቶችን አካቶ ኦዲት የሚደረጉ

ግብር ከፋዮችን መረጣ በማጠናቀቅ ዝርዝር መረጃውን ኦዲቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ለዋናው መ/ቤት ለታክስ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት እና ለሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች ወቅቱን ጠብቆ ሊተላለፍ ይገባል፡፡ የዋናው መ/ቤትም በተላለፈለት መረጃ መሰረት ስራው ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

72. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መራጭ ኮሚቴው አጠቃላይ ሪፖርቱን እና የተመረጡትን ዝርዝር አባሪ በማድረግ ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ እንደሚያስተላልፍ በተጨማሪም ለዋናው መ/ቤት የታክስ መረጃ ማደራጃና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መረጃ እንዲሰበሰብ ሲባል ዝርዝሩ የሚላክ መሆኑን፣ ለሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ግን በዝርዝሩ ወይም በእያንዳንዱ ፋይል ላይ የሚወስዱት እርምጃ ስለሌለ የመረጣ ኮሚቴው ሪፖርት(የመረጣውን ሂደት እና በየኦዲት አይነቱ የተመረጡትን ብዛት የሚያሳይ) የሚላክ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የምዕራብ እና የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች ግን ለጥያቄው ምላሽ አልሰጡም፡፡

73. ይሁን እንጂ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከ2002-2005 ባሉት በእያንደንዱ የበጀት ዓመታት ኦዲት እንዲደረጉ የተመረጡት የግብር ከፋይ ማህደራት፣ የተመረጡበት ምክንያት/የተለየ ስጋት፣ የተሰጣቸው የስጋት ደረጃ እና እንደ የስጋት ደረጃው የተወሰደውን እርምጃ (action) ማለትም የተከናወነውን የታክስ ኦዲት ዓይነት ወይም ሌሎች ተግባራት የሚያሳይ ተጠናቅሮ የተያዘ ዝርዝር መረጃ በቅ/ጽ/ቤቶቹም ሆነ በዋናው መ/ቤት ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

74. በመሆኑን የዋናው መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወነውን የታክስ ኦዲት ተግባር ባግባቡ ስለመሰራቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በተቋም ደረጃ የጠራና የተደራጀ የታክስ ኦዲት መረጃ እንዳይያዝ አድርጓል፡፡

**ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

75. የኦዲት ስራ አፈፃፀም ደረጃውን የጠበቀና የንግዱን እንቅስቃሴ ተከትሎ ክህሎቱ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት በተቋም ደረጃ

ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲተሮች ሊመሩ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

76. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራትን /ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች የመደልደሉን ተግባር በምን መልኩ እንደሚያከናውኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት እየተሰራበት የሚገኘው አሰራርን በተመለከተ ቡድን አስተባባሪው ለቡድኑ የተመደቡትን ግብር ከፋዮች የተሰማሩበትን የንግድ ዘርፍ የውስብስብነት ደረጃ ቀደም ሲል ኦዲት ከተደረገ ከፋይል በማጣራት፣ አብዛኛው የከፍተኛ ግብር ከፋይ ኦዲት በሁለት ኦዲተር የሚሰራ በመሆኑ በቡድኑ ውስጥ ያለውን የሰው ሃይል ስብጥር ኦዲተሮቹ ያላቸውን ልምድና ብቃት መሰረት በማድረግ እንደሆነና አልፎ አልፎ ኢንቨስትጌሽን ኦዲት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥም ከየቡድኑ የተውጣጡ ኦዲተሮች እንዲሰሩት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

77. ነገር ግን እያንዳንዱ ቡድን በግብር ዘመኑ ውስጥ ኦዲት እንዲደረጉ የተመደቡ ግብር ከፋዮችን ለኦዲተሮች የሚመደቡበት መስፈርት በመመሪያ ያልተቀመጠ ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ የተጠየቀውን መሰረት በማድረግ ለ2006 በጀት ዓመት ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን ለየቡድኑ ድልድል ለማድረግ የሚያስችል የመነሻ ሰነድ መዘጋጀቱንና ድልድሉም በዚሁ መሰረት መከናወኑን ገልፀዋል፡፡ የኦዲት ቡድኑም የመነሻ ሰነዱ መዘጋጀቱን አረጋግጧል፡፡

78. የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት አስቀድሞ የነበረው አሰራር፣ ማህደራቱ ከስጋት ስራ አመራር ቡድኑ ወደ ታክስ ኦዲት ስራ ሂደት ከመጣ በኋላ የስራ ሂደቱ ፣ ድርጅቱ የተመሰረተበት ጊዜ፣ የሽያጭ መጠን አልፎ አልፎ የሥራ ዘርፉ ከስጋት ስራ አመራር ሲላክ የተገለጹ ክራይቴሪያዎችን በማካተት የድልድል ስራው የሚከናወን መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ግን የሥጋት ሥራ አመራር ቡድኑ መረጣውንም ሆነ ለየቡድን የማከፋፈል ሥራውን እንደሚያከናውንና እያንዳንዱ ቡድንም በስሩ ላሉ ኦዲተሮች የኦዲተሮችን አቅም፣ የስራውን ውስብስብነት የመሳሰሉትን በመጠቀም እንደሚያከፋፍል በተጨማሪም በአብዛኛው በተለይ በስጋት የተመረጡ ማህደራት የኦዲት ሥራ የሚከናወነው ልምድ ያለው ሰራተኛ ከአዳዲስ ሰራተኞች ጋር በማጣመር በመሆኑ ሁሉም ሰራተኛ ተመሳሳይ ሥራ እንዲለምድ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

79. የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ቀላል መካከለኛና ውስብስብ ኦዲቶች በኦዲተሮች ደረጃ ማለትም ጀማሪ ኦዲተር፣ ኦዲተርና ከፍተኛ ኦዲተር በመለየት እንደሚሰራ ቡድን መሪው እና እንዳስፈላጊነቱ ወይም ውስብስብነቱ የስራ ሂደቱ አስተባባሪ ተገቢውን ክትትል እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

80. ይሁን እንጂ፣ ለየስራ ሂደቱ የተደለደሉለትን የግብር ከፋይ ማህደራት ለየቡድን አስተባባሪዎች እንዲሁም የቡድን አስተባባሪዎችም በተዋረድ ለእያንዳንዱ ኦዲተር(ኦዲተሮች) የሚደለደልበት ወይም የሚከፋፍልበት ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው የስራውን ውስብስብነት፣ ግብር ከፋዩ የተሰማራበትን ዘርፍ፣ የቡድኑን ወይም የኦዲተሩን እውቀትና ክህሎት ወ.ዘ.ተ መሰረት ያደረገ ወጥ የሆነ መስፈርት እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

81. ስለጉዳዩ የሚመለታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እስከዛሬ ድረስ ኦዲት የሚደረጉ ማህደራት ለባለሙያዎች የሚደለደልበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተደራሽ አለመደረጉን፣ ነገር ግን አሁን በዝግጅት ላይ ያለው የኦዲት ማንዋል አካቶ እንዲይዝ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

82. በመሆኑም በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወነው ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራትን /ኦዲት ኬዝ/ በየደረጃው የመደልደሉ ወይም የማከፋፈሉ ስራ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው እንዲሁም ወጥ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት/ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች የመደልደሉ ሂደት ባግባቡ እየተካናወነ ስለመሆኑ በሚመለከተው አካል ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**ከኦዲት ኬዝ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣**

83. ኦዲት እንዲደረጉ ከተመረጡ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

84. በባለስልጣን መ/ቤቱ በተዘጋጀው የህግ ማስከበር የስራ ሂደት ማንዋል ላይ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደትን በተመለከተ የስጋት ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ ቀረጥና ታክስ ኦዲት እንዲደረግ የተላለፉ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል ሊወጣ እንደሚገባ፣ በወጣው ቅደም ተከተል መሰረትም የኦዲት እቅድ ሊዘጋጅና ለኦዲተሩ ሊመራ እንደሚገባ፣

በተጨማሪም ስራውን ለኦዲተሩ ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዲቻል የኦዲት ዕቅዱ በሚዘጋጅበት ወቅት ስራው መች እንደሚሰራ፣ በማን እንደሚሰራ፣ የት እንደሚሰራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ እና ትኩረት የሚሰጣቸው ጭብጦች ምን እንደሆኑ ሊያካትት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በአጠቃላይ ዓመታዊ እና ወርሀዊ የኦዲት እቅድ ሲዘጋጅ እቅዱም ሆነ የድርጊት መርሀ ግብሩ በተዋረድ በየደረጃው እየተዘጋጀ በቡድኑም ሆነ በስራ ሂደቱ የሚጸድቅና ክትትሉም የሚከናወን መሆኑን፣ በተጨማሪም በየሳምንቱ እና በየወሩ የየቡድኑ እንዲሁም የሥራ ሂደቱ እቅድ አፈጻጸም እንደሚገመገም ለዚህም የቢ.ኤስ.ሲ.(ባላንስድ ስኮር ካርድ) እቅድ፡ የድርጊት መርሀ ግብር በየቀኑ እያንዳንዱ ኦዲተር የሚሰራው ስራ እየተያዘ የሚገመገምበት አሰራር መኖሩን ገልፀዋል፡፡

86. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ፣ በቡድን አስተባባሪ ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር እንደሚዘጋጅ እና በድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት ኦዲት ሲጀመር ለእያንዳንዱ ኦዲት፣ ኦዲት ፕሮግራም በማዘጋጀት ለስራ ሂደቱ እንደሚቀርብ፣ ነገር ግን የተቋሙ ዋና ስራ ኦዲት ባለመሆኑ በተቋሙ ከዚህ በላይ የስራ ሂደቱን አልፎ እንደማይሄድና የስራ ሂደቱ በፕሮግራም መሰረት መሰራቱን አይቶ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ እንደሚፈርም ገልፀዋል፡፡

87. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የተከናወኑ ኦዲቶች የስራ ወረቀት በተከለሰበት ወቅት ኦዲቱ በአግባቡ መከናወኑን ለመከታተል የሚያስችል ቼክ ሊስት እና በየደረጃው የተደረገውን የኦዲት ክለሳ/audit review/ የሚያሳይ መረጃ ለማግኘት አልቻልንም፡፡ በተጨማሪም በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከ2002-2005 በጀት ዓመታት የተከናወኑ ኦዲቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ የታክስ ኦዲት ቡድን ለቡድኑ የተመሩትን እያንዳንዱን የግብር ከፋይ ማህደራት በተሰጣቸው የስጋት ደረጃ መሰረት ቅደም ተከተል በማውጣት ኦዲት የሚያደርግበትን ጊዜ/ኦዲቱ የሚጀመርበት እና ኦዲቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ/፣ ኦዲቱ በማን እንደሚከናወን፣ የኦዲት ሂደት እና ሌሎች የኦዲት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የተዘጋጀ እና የፀደቀ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር/ኦዲት ፕሮግራም እንዲሁም የኦዲት ቡድን አስተባባሪውም ሆነ የስራ ሂደቱ እያንደንዱ ኦዲቶች በታቀደላቸው ወቅት፣ የጊዜ ተመን

እና የኦዲት ሂደት መሰረት የተከናወኑ ስለመሆኑ የተደረገ ክትትል እና የአፈፃፀም ግምገማ የተጠናቀረ ማስረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

88. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በየኦዲት አይነቱ ኦዲት እንዲደረጉ የተለዩ ማህደራት የትና መቼ ኦዲት እንደሚደረጉ በቅ/ጽ/ቤቶቹ የኦዲት የስራ ሂደት ይታወቃል የሚል እምነት እንዳላቸው፣ ኦዲት የሚደረጉ ማህደራት በኦዲት ቡድን አስተባባሪዎችና በኦዲት የስራ ሂደት ክትትል የሚደረግ እንዲሁም በስራ ሂደት ውስጥ የተደራጀው የ1ለ5 አደረጃጀት በኦዲት ባለሙያዎች በኩል የውሎ ግምገማ እንዲሁም በስራ ሂደት በኩል በየሳምንቱ የስራ ግምገማ ስለሚደረግ ኦዲት በመደረግ ላይ ያሉ ፋይሎች ክትትልና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በዋናው መ/ቤት በኩል በሚደረግ ድጋፍና ክትትልም እንደ አንድ አጀንዳ በቢ.ጋር/ቼክ ሊስት/ ውስጥ ተካቶ አፈፃፀሙን እየተከታተሉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በባለስልጣን መ/ቤቱ አደረጃጀትና መዋቅር ሰነድ ላይ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከሚደረገው የክትትልና ቁጥጥር በተጨማሪ የታክስ ኦዲት አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በቅ/ጽ/ቤቶች በዕቅድ የተቀመጡትን የኦዲት ሥራዎች በታቀደው መሰረት እየተፈጸሙ መሆኑን በመከታተል ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ መስጠት እንዲሁም የኦዲት ስራ አፈፃፀም ደረጃውን የጠበቀና የንግዱን እንቅስቃሴ ተከትሎ ክህሎቱ ባላቸው ባለሙያዎች እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

89. በመሆኑም ለእያንደንዱ ኦዲት፣ የኦዲት ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የተዘጋጀ እና የፀደቀ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር/ኦዲት ፕሮግራም እንዲሁም እያንዳንዱ ኦዲት በታቀደለት ወቅት፣ የጊዜ ተመን እና የኦዲት ሂደት መሰረት የተከናወነ ስለመሆኑ የተደረገ ክትትል እና የአፈፃፀም ግምገማ የተጠናቀረ መረጃ የማይያዝ በመሆኑ የተከናወኑት ሁሉም ኦዲቶች የስጋት ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ ቅደም ተከተል የወጣላቸው፣ በወጣው ቅደም ተከተል መሰረትም ኦዲቱ የተከናወነ በተጨማሪም ስራው መች እንደተሰራ፣ በማን እንደተሰራ፣ የት እንደተሰራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ እና ትኩረት የሚሰጣቸው ጭብጦች በሚገባው መጠን የተዳሰሱ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

**የሚከናወኑ ሁሉም ኦዲቶች ወጥነት ያላቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ለኦዲት ስራው አጋዥ የሆኑ ፎርማቶችን ማዘጋጀትን በተመለከተ፣**

90. እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበት አሰራሮች በኦዲት ስራ ወረቀቶች የተደገፉ እንዲሁም በኦዲተሮች የተዘጋጁት መግለጫዎችና ሌሎች ሰነዶች ተፈርመው ከኦዲት ውጤቱ ማጠቃለያ ጋር ለስራ ሂደቱ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ የኦዲት ስራ ወረቀቶቹም ባግባቡ ሊደራጁ (ግልፅ እና የተሟሉ) እና በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችሉ መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ ሊደረጉ ይገባል፡፡

91. ስለጉዳዩ በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የኦዲት ሥራ ወረቀቶችን በተመለከተ ለእያንዳንዱ ኦዲት የሚዘጋጅና የሚያዝ የኦዲት የስራ ወረቀት ማህደር/ፋይል እንደሌለና ለእያንዳንዱ ኦዲት የሚዘጋጁት የኦዲት ሥራ ወረቀቶች በኦዲት ተደራጊው ግብር ከፋይ ማህደር ላይ ተያይዘው እንደሚቀመጡ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን በተለየ መልኩ ተዘጋጅተው በሥራ ሂደት ደረጃ መቀመጥን በሚመለከት ከላይ እንደተገለጸው የተሟላ ኦዲት ሊይዛቸው የሚገቡ የኦዲት ሥራ ወረቀቶች/ፎርማቶች በቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅተው ለቅ/ጽ/ቤቱ እንዲሁም ለዋናው መ/ቤት ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የቀረቡ ቢሆንም፣ በተቋም ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የኦዲት ማንዋል እየተዘጋጀ እንደሆነ በመገለፁ ምክንያት እስካሁን ተግባራዊ እንዳልተደረገና፣ ነገር ግን መሰረታዊ የሆኑ ቅጾችን እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

92. የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ቅ/ጽ/ቤቱ አሁን ወደሚገኝበት ሕንፃ ከተዛወረበት ጀምሮ (ከሐምሌ/2003 ዓ.ም.) አንድ ክፍል በማዘጋጀትና የጽ/ቤት ረዳት በመመደብ የኦዲት የስራ ወረቀቶች በኃላፊነት እንዲያዙ መደረጉን የገለፁ ሲሆን፣ የኦዲት የስራ ወረቀቶችን ወጥነት በተመለከተ በቅ/ጽ/ቤቱ በተካሄደው የ2005 በጀት ዓመት የስራ ሂደት የስራ አፈፃፀም ግምገማ ወቅት ችግሮች መኖራቸው የታየ በመሆኑ በቀጣይ ይህን ለማስተካከል እንደ ሪፈረንስ የሚያገለግል አንድ የኦዲት የስራ ወረቀት በ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት ለማዘጋጀት እየሰሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

93. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የኦዲት መስሪያ ወረቀቶች፣ የመውጫ ውይይት በየጊዜው እየተቀየረ አስተያየት የሚሰጥባቸው ሳይሆኑ ከማንዋል ጋር አብረው የተቀረፁ መሆናቸውን እና ስራ ላይም እየዋሉ እንደሚገኙ እና ኦዲተሮችም ለእያንዳንዱ ስራ በዚያው አግባብ መስራታቸው ክትትል እንደሚደረግና እንደሚረጋገጥ በተጨማሪም የተሰራባቸው የኦዲት የስራ ወረቀቶች የሪፖርት አካል መሆናቸውንና ይህም ኦዲት በተደረጉ የግብር ከፋይ ፋይሎች/ማህደሮች ውስጥ፣ ኦዲቱን ባከናወኑ ኦዲተሮች፣ በቡድን መሪ እና በስራ ሂደት ኮፒዎች ተሰራጭተው እንደሚቀመጡ ገልፀዋል፡፡

94. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች እና የኦዲት መስሪያ ወረቀቶች በናሙና በተከለሱበት ወቅት ወጥነት የሌላቸው እና ባግባቡ ተጠቃቅሰው እና የመዝገብ ቁጥር እንዲሰጣቸውና ተመዝግበው እንዲቀመጡ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የኦዲት ሪፖርቶችና የመስሪያ ወረቀቶች ይዘት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በተመለከተ ክትትል ለማድረግ ኃላፊነት በተሰጣቸው ሰዎች በየደረጃው የተደረገ የማረጋገጥ ስራ ስለመሰራቱ የሚያስረዳ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

95. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኦዲት መስሪያ ወረቀቶች ወጥ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተው ለሪፖርት ማጣቀሻነት ማገልገል እንደሚገባቸው የሚታወቅ ቢሆንም፣ እነዚህ የሰራ ወረቀቶች በአንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች እንደ ኦዲተሩ የግል ንብረት የሚቆጠሩበት ሁኔታ እንዳለ የድጋፍና ክትትል ተግባር ባከናወኑበት ወቅት ያረጋገጡ መሆኑንና ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል የኦዲት የስራ ወረቀቶች በማዕከላዊነት በስራ ሂደቱ ግልፅና በሚፈለግ ጊዜ በቀላሉ ሊገኝ በሚችልበት ሁኔታ እንዲቀመጥ ለማድረግ በግብረ መልስ ሪፖርት ያስተላለፉበት ሁኔታ ቢኖርም በቀጣይ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን ለማመላከት በሚያስችል መለኩ እንዲተገበር ለማስቻል በዝግጅት ላይ ያለው የኦዲት ማንዋል መሰረታዊና ለኦዲት ስራ አስፈላጊና የማይቀየሩ ናቸው ያላቸውን የስራ ወረቀቶች አካቶ እንዲያዝ የተደረገ መሆኑንና ባለው አሰራር የሚከናወኑ የኦዲት መስሪያ ወረቀቶች በተገቢው መንገድ ተደራጅተው እንዲያዙ በዳይሬክቶሬቱ ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

96. በመሆኑም እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበትን አሰራሮች ተከትሎ የተከናወነ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አላስቻለም፡፡ የኦዲት ስራ ወረቀቶችም ማህደር ተዘጋጅቶላቸውና ባግባቡ ተደራጅተው (ግልፅ እና የተሟሉ) በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችል መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ ባለመደረጉ የታክስ ኦዲት እንዴት እንደሚካሄድና ኦዲቱ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በማጥናት መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን አሰራሮች ለማሻሻል እና ለአዳዲስ ኦዲተሮች ስለአሰራሩ ለማሳየት ካለማስቻሉ በተጨማሪ የታክስ ኦዲት ተቋማዊ አሰራር ግልፅና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን አያስችልም፡፡

**በቅድመ ኦዲት ዝግጅት የግብር ከፋዩን መብትና ግዴታ በግልጽ ማሳወቅን በተመለከተ፣**

97. የታክስ ኦዲት ከመከናወኑ በፊት፣ በኦዲቱ ወቅት እና ከኦዲቱ በኃላ ግብር ከፋዮች ስላላቸው መብትና ግዴታ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

98. የታክስ ኦዲት ተግባርን ግልፅነት እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለማከናወን እንዲቻል እያንዳንዱ የታክስ ኦዲት ከመከናወኑ በፊት፣ በኦዲቱ ወቅት እና ከኦዲቱ በኃላ ግብር ከፋዮች በኦዲቱ ላይ ስላላቸው መብትና ግዴታ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መደረግ እንዳለበት በታክስ ኦዲት ፖሊሲው ላይ ተቀምጧል፡፡

99. በመሆኑም እያንዳንዱ የስራ ሂደት የኦዲት ስራውን ከመጀመሩ በፊት ወይም የኦዲት ዝግጅቱን አጠናቆ የኦዲት ስምሪቱን ሲጀምር፣ በኦዲት ፕሮግራሙ መሰረት ኦዲት ተደራጊው ድርጅት ወይም ኩባንያ ስላላቸው መብትና ግዴታ፣ መቼ ኦዲቱ እንደሚደረግ፣ ለምን ኦዲቱ እንደሚደረግና በማን ኦዲቱ እንደሚደረግ ድርጅቱም ይህንኑ ተገንዝቦ በታክስ ህጉ መሰርት ለኦዲት ስራ የሚያገለግሉ አስፈላጊ ሰነዶችን በወቅቱ እንዲያዘጋጅና ድርሻውን እንዲወጣ በአጠቃላይ ድርጅቱ በኦዲት ሂደት ውስጥ ስላሉት መብትና ግዴታዎች ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

100. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ማንኛውም የኦዲት ሥራ ከመከናወኑ አስቀድሞ የኦዲት ቃለ መጠይቅ ከኦዲት ተደራጊው ግብር ከፋይ ጋር የሚደረግ መሆኑን እና ይኸውም ወጥ ሆኖ በተቀረጸ ማንኛውም የኦዲት ሥራ ከመከናወኑ በፊት የሚሞላና በግብር ከፋዩ ማህደር ላይ እንደሚታሰር ገልፀዋል፡፡

101. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በስጋት መስፈርት የተመረጡና የኢንቨስትጌሽን ኦዲት በሚካሄድበት ወቅት ከቅድመ ዝግጅት አንደኛውና ዋናው ኦዲት ተደራጊው ግብር ከፋይን ስለኦዲቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት እንደሆነ ይኸውም በስራ ሂደቱ አስተባባሪ የተፈረመ ደብዳቤ እንደሚፃፍ እና በቀጣይ የመግቢያ ጥያቄና ውይይት እንደሚካሄድ በተጨማሪም ኦዲቱን የሚሰሩት ኦዲተሮችና ግብር ከፋይ በመፈራረም ኦዲቱ የሚጀመርበት ቀን፣ የሚከናወንበት ቦታ፣ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ወዘተ በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ውይይትና መግባባት ከተደረሰ በኃላ ስራው እንደሚጀመር ገልፀዋል፡፡

102. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የግብር ውሳኔዎች የቅሬታቸው መነሻ ምን እንደሆነ ለማወቅ በቅ/ጽ/ቤቱ ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ቡድን የግብር አቤቱታ ውሳኔዎች ላይ በ07/02/2005 ዓ.ም. የተካሄደ ጥናት ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ዋና ዋና ችግሮች ተብለው ከተለዩት መካከል፡-

<u>የደንበኞች ችግር</u>

- ✓ ግብር ከፋዩ በኦዲት ወቅት መረጃ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ፣ ለማምጣት ፈቃደኛ አለመሆን ነገር ግን ውሳኔው ከደረሰው በኃላ ሰነዱን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በማቅረብ እንዲታይለት እንደሚጠይቅ፣
- ✓ የደንበኛው የግንዛቤ እጥረት እና ጊዜን በአቤቱታ ገዝቶ እፎይታ ለማግኘት እና ሲቆይ ምህረት ይደረግልኛል በሚል በተሳሳተ አሰተሳሰብ ቅሬታ እንደሚያቀረብ፣
- ✓ ግብር ከፋዩ መቀጫ በግብር አወሳሰን አሰባሰብ የስራ ሂደት በመመሪያው መሰረት ከተነሳላቸው በኋላ ቀሪው ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳላቸው ጥያቄ እንደሚያቀርብ፣

<u>የባለስልጣኑ ችግር</u>

- ✓ ይርጋ የሚገቡ ድርጅቶችን በአግባቡ ዕቅድ አውጥቶ ጊዜው ሳይደርስ ከመወሰን ይልቅ የይርጋ ጊዜው ሲቃረብ ሙሉ መረጃ ሳያገኙ እና መውጫ ስብሰባ /Exit Conference/ ሳያካሄዱ መወሰን፣
- ✓ ለግብር ከፋዩች በወጡት አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች እንዲሁም አዳዲስ በሚወጡ ማሻሻያዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውስንነት መኖር፣

- ✓ ድርጅቱ/ግብር ከፋዩ አቤቱታ ለማቅረብ ሲመጣ ትክክለኛ መንገድን አለማሳየት እና አቤት እንዲል ክፍተት መፍጠር፣
- ✓ በትክክለኛ የኦዲት ፕሮግራም እንዲሰራ ያለማድረግ ችግር፣
- ✓ ውሳኔ ከመውጣቱ በፊት ከግብር ከፋዩ የሚመለከተው አካል ጋር በትክክል ያለመወያየት፣
- ✓ የዴስክ ኦዲት ተደርገው የከፈሉትን በአጠቃላይ ኦዲት ሲወሰን ተቀናሽ አለማድረግ የሚሉት መኖራቸው ተገልጿል፡፡

103. በመሆኑን ግብር ከፋዮች ስላላቸው መብትና ግዴታ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል በኦዲት ወቅት ከግብር ከፋዩ እና ከባለስልጣን መ/ቤቱ የሚጠበቁ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ አስገዳጅነት ያለው ሰነድ/የግብር ከፋይ ቻርተር/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉንና ግብር ከፋዮችም በሚፈለገው መጠን የጠራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማይደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

104. ግብር ከፋዮች በኦዲት ወቅት ለኦዲት ስራ የሚያገለግሉ አስፈላጊ ሰነዶችን በወቅቱ የማያቀርቡ በመሆኑ ኦዲቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ በተጨማሪም በግብር ከፋዮ የግንዛቤ እጥረት አንዳንዴም በተሳሳተ አሰተሳሰብ አብዛኛው የኦዲት ውሳኔዎች ወደ አቤቱታ እንዲሄዱና መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ አድርጓል፡፡

### በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት የኦዲት መተማመኛ ስርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን በተመለከተ፣

105. ከግብር ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ በመቀነስ በተቻለ መጠን በልዩነት በሚወሰነው ግብር/ታክስ ላይ በመተማመን ያለ አቤቱታ የሚከፈልበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት የመውጫ ስብሰባ(Exit conference) በማዘጋጀት በኦዲት ውጤት ላይ ውይይት ሊደረግ ይገባል፡፡

106. በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት የመውጫ ስብሰባ በማዘጋጀት በኦዲት ግኝቶች/ውጤት ላይ ውይይት መደረግ እና ከግብር ከፋዩ ጋር ስምምነት ላይ መደረስ እንዳለበት የኦዲት ደረጃ ስታንደርድ ያዛል፡፡

107. ኦዲተሮች የመጨረሻውን የኦዲት ውሳኔ ከማውጣታቸው በፊት/በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት በእያንዳንዱ የኦዲት ግኝቶች ላይ ከግብር ከፋዩ ጋር ስምምነት እንዲደርሱ ወይም በውሳኔው ላይ ስለመስማማቱ/አለመስማማቱ በግልጽ በሚያሳይ ማስረጃ/በቃለ

ጉባኤ በማስደገፍ ለሁሉም ኦዲቶች እንዲያዝ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ በናሙና የታዩት ሦስቱም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ማንኛውም የኦዲት ሥራ ሲጠናቀቅ ውሳኔው ከመውጣቱ አስቀድሞ ከኦዲት ተደራጊው ድርጅት ጋር የኦዲት መተማመኛ የመውጫ ውይይት የሚደረግ እና ይህም በግብር ከፋዩ ማህደር ላይ የሚታሰር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

108. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በናሙና ተመርጠው ከተከለሱት የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤዎች ውስጥ አንዳንድ የኦዲት ውሳኔዎች ወደ አቤቱታ የሚቀርቡት ኦዲተሮች ስለኦዲት ግኝቱ በስብሰባም ሆነ በኦዲት ጊዜ ምንም ጥያቄ ሳያቀርቡና መተማመን ላይ ሳይደረስ የኦዲት ውሳኔ የሚደርሳቸው መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

109. በተጨማሪም በከፍተኛ ግብር ከፋዮች እና በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች፣ በቅ/ጽ/ቤቶቹ በተወሰነ መልኩ የተከናወኑ የግብር/ታክስ አቤቱታ ውሳኔዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ሰነድ በተከለሰበት ወቅት አብዛኞቹ የግብር ውሳኔዎች እንዲስተካከሉ የሚደረጉት ግብር ከፋዩ በኦዲቱ ወቅት ያላቀረበውን መረጃ በማቅረቡ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

110. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ እያንዳንዱ ኦዲት ሲጠናቀቅ የውሳኔው ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት የመውጫ ስብሰባ የሚደረግ መሆኑን፣ ነገር ግን ግብር ከፋዩ ውሳኔውን ለማዘግየት ሲል የመውጫ ስብሰባ ላይ በቀጠሮ መሰረት አለመገኘት እንዲሁም የመውጫ ሰብሰባ አካሂዶ ቅጹን ለመሙላት አለመፈለግ የመሳሰሉ አንዳንድ ሁኔታዎች እንዳሉ በየቅ/ጽ/ቤቱ ያሉ የኦዲት የስራ ሂደቶች የሚገልፁበት ሁኔታ እንዳለ የተመለከቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የመውጫ ስብሰባ ላይ በግብር ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው በኩል እንዲገኙ የሚገባቸው አካላትን በሚመለከት ወጥ በሆነ መልኩ የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ በየቅ/ጽ/ቤቱ ጉራማይሌ በሆነ መልኩ ሲተገበር እንደሚስተዋልና በቀጣይ በሁሉም ዘንድ ወጥ የሆነ ተደራሽነት እንዲኖረው በግብር ከፋዩ እንዲሁም በኦዲት አድራጊው በኩል እነማን መገኘት እንደሚገባቸው የሚያስረዳ ዝርዝር በዝግጅት ላይ ያለው ማንዋል እንዲያካትት ስለተደረገ ለወደፊቱ ወጥ ይሆናል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

111. በመሆኑም ኦዲተሮች የመጨረሻውን የኦዲት ውሳኔ ከማውጣታቸው በፊት/በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት በእያንዳንዱ የኦዲት ግኝቶች ላይ ከግብር ከፋዮች ጋር የመውጫ ስብሰባ በማካሄድ ስምምነት እንዲደርሱ ባለመደረጉ እና ኦዲት ተደራጊው ግብር ከፋይም በውሳኔው ላይ ስለመስማማቱ/አለመስማማቱ በግልጽ በሚያሳይ ማስረጃ/በቃለ ጉባኤ በማስደገፍ ለሁሉም ኦዲቶች እንዲዘጋጅና እንዲያዝ ባለመደረጉ ከተከናወኑ ኦዲቶች አብዛኞቹ ወደ አቤቱታ የሚሄዱ፣ በአቤቱታው ውሳኔ መሰረትም አብዛኞቹ እንዲስተካከሉ የሚደረግ በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱን ለተጨማሪ ጊዜና ወጪ እየዳረጉት ይገኛሉ፡፡

**ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣**

112. በታክስ ኦዲት ወቅት በግብር ከፋዩ ከሚቀርበው መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ መረጃዎቹም በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

113. በባለስልጣን መ/ቤቱ በተዘጋጀው የ2003-2007 ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ በዋነኛነት ያሉና የተጀመሩ የመረጃ ሥርዓቶችን በማጠናከርና ሙሉ በሙሉ በመጠቀም ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ለመፈፀም በዋነኛነት ከሚከናወኑ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችና ዋና ዋና ተግባራት መካከል ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ የመረጃ አሰባሰብ፣ ጥንቅርና ሥርጭት፣ አጠቃቀምና ግብረ-መልስ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ተቀምጧል፡፡

114. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

115. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት፡-

- ✓ በኦዲት ወቅት ግብር ከፋዩ ከሚያቀርበው የኦዲት ሰነዶች በተጨማሪ በሲስተም የሚገኙ መረጃዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ እንደሆነና ድርጅቱ በጥቆማ፣ በኢንተለጀንስ እንዲሁም በመሳሰሉት ምክንያቶች ኦዲት የሚደረግ ከሆነ ደግሞ ኦዲቱ እንዲከናወን ከጠየቀው አካል ተጨማሪ መረጃ ከቀረበ ይኸው በግብዓትነት የሚጠቀሙበት መሆኑን፣ በተጨማሪም ኦዲት በሚደረጉ ድርጅቶች ላይ ኦዲተሩ

ማንኛውንም አይነት ተጨማሪ መረጃ ከፈለገ ይኸው ከሚመለከተው አካል በደብዳቤ ተጠይቆ እንዲመጣ እንደሚደረግ፣

- ✓ ኦዲት የሚደረገው ድርጅት የተለያየ አገልግሎት ጠይቆ ኦዲት የሚደረግ ከሆነና ለዚህም የሚያስፈልግ መረጃ ካለ በተመሳሳይ የሚጠየቅ ሲሆን ድርጅትን ለመዝጋት ወይንም ለማፍረስ በሚጠየቁ አገልግሎቶች ምክንያት የሚከናወኑ የኦዲት ሥራዎችን በተመለከተ ግን ከታክስ መረጃ ዳይሬክቶሬት ስለድርጅቱ መረጃ ከተጠየቀና የዚሁ ምላሽ ተጠናቅሮ ከመጣ በኋላ ብቻ የኦዲት ስራው የሚከናወን መሆኑን፣
- ✓ ከ2002-2005 በጀት ዓመታት በተከናወኑ የኦዲት ሥራዎች በሶስተኛ ወገን የተገኘ ተጨማሪ ገቢ የተገኘው መረጃ ተጠናቅሮ በስራ ሂደቱ የሚያዝበት አሰራር አለመኖሩን፣

116. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት ደግሞ፣

- ✓ የስራ ሂደቱ በአወሳሰን ቡድን አማካኝነት ግብር ከፋዩ ከሚያቀርበውና በሲግታስ ላይ የሚታየውን ልዩነት ብቻ ከመወሰን ተላቆ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የሦስተኛ ወገን መረጃን ተጠቅሞ በውስን የሂሳብ ምርመራ ሂደት/ዴስክ ኦዲት/ ግብርን የሚወስን መሆኑን፣ በተጨማሪም ኦዲተሩ ሙሉ ኃይሉን በሥጋት መሥፈርት በተመረጡት ላይ ብቻ እንዲያውል ለማስቻል በዴስክ ኦዲት አማካኝነት ውሳኔ የተሰጣቸው እና ተጨማሪ ዝርዝር ስራ ሊከናወንባቸው የሚገቡትን ግብር ከፋዮች በአጠቃላይ ኦዲት እንዲታዩ ወደ ታክስ ኦዲት የስራ ሂደት እንዲተላለፉ እንደሚያደርግ፣
- ✓ ዴስክ ኦዲትን በተመለከተ 2000-2004 ዓ.ም ከሶስተኛ ወገን የተላከ መረጃ ስሌለለ የተሰራ ስራ አለመኖሩን ነገር ግን የ2005 በጀት አመት የውጭ አገር አሰሪና ሰራተኛ አገኛኝ ኤጀንሲ ከኢንተለጀንስ ቡድን የተላከ መረጃን መሠረት በማድረግ የ7 ድርጅቶች የዴስክ ኦዲት መሰራቱ ተገልጿል፡፡

117. በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት ደግሞ ከሶስተኛ ወገን ተደራጅቶ የተገኘው እና የተጠቀሙበት መረጃ በASYCUDA የሚተላለፈውን መረጃ መሆኑን ይህም ደግሞ ተለይቶ የተያዘ መረጃ እንደሌለው ገልፀዋል፡፡

118. ይሁን እንጂ በታክስ ኦዲት ወቅት ከግብር ከፋይ ከሚቀርብ መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠናቅረው እንደማይያዙ ወይም እንደማይሰበሰቡ እና በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደማይውሉ ታውቋል፡፡

119. በተጨማሪም ተቋሙ የሶስተኛ ወገን መረጃ በመጠቀም የሚያከናውናቸው የአሰስመንት ሥራዎች ውጤታማ እንደሆኑ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በቅ/ጽ/ቤቶቹ በየበጀት ዓመታቱ የሶስተኛ ወገን መረጃን በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ በማዋል የተገኘ ተጨማሪ ግብር/ገቢ መረጃ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

120. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከታክስ መረጃ ዳይሬክቶሬት የሚጠበቀው የግዥና ሽያጭ መረጃዎች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃዎችና እንዲሁም የጉምሩክ መረጃዎች ከአሲኩዳ ለኦዲተሮች በመረጃ ቴክኖሎጂ በኩል ስለሚገኙ በወቅቱ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲጠቀሙበት የሚደረግ መሆኑን፣ ይህ ማለት ግን በአጠቃቀም ላይ ችግሮች የሉም ማለት እንዳልሆነና በቀጣይ እየፈተሹ የሚያስተካክሉት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

121. በመሆኑም በቅ/ጽ/ቤቶች በአንዳንድ የኦዲት ስራዎች ወቅት የሶስተኛ ወገን መረጃን የመጠቀም ሁኔታ ቢኖርም በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠናቅረው የማይያዙ/የማይሰበሰቡ እና በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ የማይውሉ እንዲሁም መረጃዎቹ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትል ለማድረግ የሚያስችል በአግባቡ የተዘረጋ አሰራር ባለመኖሩ በግብር ከፋዩ የሚቀርቡ የታክስ ማስታወቂያዎችና ሌሎች መረጃዎች ትክክለኛነትን በአግባቡ ለማረጋገጥ ካለመቻሉ በተጨማሪ መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ በሚፈለገው መጠን መሰብሰብ ወይም አለመሰብሰቡን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣**

122. በተከናወኑ የኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተገቢው እርምጃም ስለመወሰዱ በየደረጃው (በዋና መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

123. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባደረጋቸው የአደረጃጀትና የመዋቅር ለውጦች መነሻ የኦዲት ስብጥሩ በየስራ ሂደቱ ማለትም አጠቃላይ ኦዲት በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት፣ ኢንቨስትጌሽን ኦዲት በህግ ማስከበር የስራ ሂደት እንዲሁም ዴስክ ኦዲት በግብር አወሳሰንና ክትትል የስራ ሂደት እንዲከናወን መደረጉ ታውቋል፡፡ በዚህም መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የኦዲት አይነቶችን በማከናወን ተጨማሪ ግብር/ታክስ፣ ወለድ እንዲሁም መቀጫ ውሳኔ በማውጣት ለግብር ከፋዮች እንዲደርሳቸው ያደረጉ መሆኑን፣ ለአብነትም በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002-2005 በጀት ዓመታት ዘጠኝ ወር ድረስ ብር 2,025,438,108.21 ተጨማሪ ፍሬ ግብር/ታክስ እና ብር 2,923,323,143.86 ወለድና መቀጫ በድምሩ ብር 4,948,761,252.07 የተወሰነ መሆኑን፣ (ዝርዝሩን ከአባሪ 2 መመልከት ይቻላል)

124. ነገር ግን ግብር ከፋዩች የመቀጫ ይነሳልኝ አቤቱታ ባቀረቡት መሰረት ከመቀጫ አነሳስ መመሪያ መሰረት ተመርምሮ ከተጣለው የመቀጫ መጠን በ2002 በጀት ዓመት የ378 ግብር ከፋዮች ከተወሰነው ጠቅላላ ብር 54,411,310.83 ውስጥ ብር 45,104,015.21 (83 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 9,307,295.62 (17 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ ፀንቷል፡፡ በ2003 በጀት ዓመት ደግሞ የ1052 ግብር ከፋዩች ከተጣለው የመቀጫ መጠን ብር 103,514,519.8 ውስጥ ብር 84,488,177.73 (82 በመቶ) ቀሪ በማድረግ ብር 19,026,342.7 (18 በመቶ) ብቻ እንዲከፍሉ የፀና መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

125. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በታክስ ኦዲት ተጨማሪ የሚወሰነው ግብርና ታክስ አሰባሰብን በተመለከተ በአንድ በጀት ዓመት የተወሰነው ግብርና ታክስ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ ቀርቦበት እንዲስተካከል ውሳኔ ከተሰጠው በኃላ በታክስ ኦዲት ተስተካክሎ በሚወጣው ውሳኔ ማስታወቂያ መሰረት የሚሰበሰብ እና/ወይም የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል የሚገባበት በመሆኑ አሰባሰቡ ከአንድ ግብር ዘመን ወደ ቀጣይ ግብር

ዘመን እንደሚዞርና በተጨማሪም በፍሬ ግብር ላይ የተጣለው መቀጫ በአስተዳደራዊ ሁኔታ የሚነሳ በመሆኑ በታክስ ኦዲት የተወሰነው በሙሉ እንደማይሰበሰብ ታውቋል፡፡

126. በተጨማሪም በቅ/ጽ/ቤቶቹ በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ ስለመወሰዱ በየደረጃው (በቅ/ጽ/ቤቶች እና በዋና መ/ቤት) ክትትል የሚደረግበትና መረጃው ተጠናቅሮ የሚያዝበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

127. የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት፣

- ✓ በእያንዳንዱ የኦዲት ዓይነቶች የተወሰኑ ማህደራትና በኦዲት የተገኘ ተጨማሪ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በተመለከተ ከ2002-2005 ድረስ በየበጀት ዓመታቱ በዝርዝርም ሆነ በጥቅል መረጃው የሚያዝ መሆኑን፣ ነገር ግን ክፍያ የፈጸሙ እንዲሁም ስምምነት የገቡ ግብር ከፋዮችን መረጃን በተመለከተ ስራው የሚከናወነው በግብር አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት እንደሆነ፣
- ✓ በኦዲት ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በተመለከተ ደግሞ የክትትል ስራውን (ማን፣ መቼ እንዳቀረበ፣ የቅሬታው ምክንያትና አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔን የሚመዘግብ የሚተነትንና መረጃ የሚያጠናቅር) ቅሬታን የሚቀበል በቡድን ደረጃ የተቋቋመ አካል በደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት ውስጥ እንደሚገኝ፣ ይሁን እንጂ ቅሬታ የሚቀርብባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮችን የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት 1ለ5 ቡድን ውይይት እንደሚያደርግባቸው እና መስተካከል ባለባቸው ጉዳዮችም ላይ በየጊዜው የማስተካከል ስራ እንደሚያከናውን እንዲሁም የኦዲት ውጤት ከአመታዊ ገቢ አንፃር በገቢ ሒሳብ በየዓመቱ የሚገለፅ መሆኑን፣
- ✓ በእያንዳንዱ ከአቤቱታ ተመልሰው የተወሰኑ ማህደራትና በኦዲት የተገኘ ተጨማሪ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በተመለከተ ከ 2002-2005 ድረስ በየበጀት ዓመታቱ በዝርዝርም ሆነ በጥቅል መረጃው የሚያዝ መሆኑን ገልፀዋል፤

128. የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት፣

- ✓ ወደ ስራ ሂደቱ የሚተላለፉ የኦዲት ውሳኔዎች ላይ በታክስ ህጉ መሰረት ተገቢው እርምጃ በወቅቱ የሚወሰድ መሆኑን በተመለከተ፣ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው ለስራ ሂደቱ እንደደረሰ 30 ቀናት ሳይሞላ የስልክ ጥሪ የሚደረግ ሲሆን፣ 30 ቀናት

ካለፈው ዕዳውን እንዲከፍል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንደሚፃፍና ደብዳቤ ተፅፎ ምላሽ ካልተሰጠ ከባንክ ሂሳብ ጀምሮ የማገድና በግብር ዕዳው መጠን ካለው ሂሳብ ላይ በቅርንጫፉ አካውንት ገቢ እንዲደረግ ደብዳቤ እንደሚፃፍ ተገልጻል። ከዚህም በተጨማሪ የድርጅቱ ቋሚ ንብረት የማገድና ንብረት ስለመኖሩ መረጃ ከተገኘ ሽያጩ እንዲካሄድ ለሚመለከተው ዳይሬክቶሬት እንዲያውቀው ተደርጎ ሽያጩ በዳይሬክቶሬቱ በኩል ተካሂዶ በቅርንጫፉ አካውንት ገቢ እንደሚደረግ የገለፁ ሲሆን፣ ነገር ግን በስራ ሂደቱ ያለው የክትትል ሰራተኛና ግብር ከፋይ በብዛት ስለማይመጣጠን ከፍተኛ የግብር ዕዳ ያለባቸውን ቅድሚያ በመስጠት ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ፣

- ✓ እስከ 2005 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውሳኔዎች ለስራ ሂደቱ ሲደርሱ በግብር አሰባሰብና ዕዳ ክትትል ቡድን በእያንዳንዱ ፈፃሚ ስም ተመዝግቦ በበጀት ዓመት በግብር ከፋይ፣ በኦዲት ዓይነት እና በግብር ዓይነት ተለይቶ ለእያንዳንዱ ፈፃሚ ለአሰባሰብ ይመራ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት መረጃውን በበለጠ ሁኔታ ለመመዝገብ በእያንዳንዱ ኦፊሰር ስም ኤክስኤል ላይ ፋይል በመክፈት የአሰባሰብ ክትትል በመሰራት ላይ እንደሚገኝ፣ ይሁን እንጂ ከ2003 እስከ 2005 በኦዲት ውጤት መሠረት በ30 ቀናት ክፍያ የፈፀሙና ንብረታቸው የተወረሰ ግብር ከፋዮች መረጃ በወቅቱ መረጃው ያልተያዘ በመሆኑ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

129. የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት፣

- ✓ በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት የውሳኔ ማስታወቂያ ወጪ ከተደረገ በኃላ ያለው የክትትል ስራ በቅ/ጽ/ቤቱ አደረጃጀት መሰረት ለግብር ከፋዩ የደረሰው የውሳኔ ማስታወቂያ ቅጂ ለግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት እንደሚሰጥና በግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት ስር የሚገኘው የግብር አሰባሰብና ክትትል ቡድን ውሳኔ ከደረሳቸው 30 ቀን የሞላቸውን፣ አቤቱታ ያቀረቡትን መረጃዎች በማጠናቀር ክትትል ስራውን በባለቤትነት የሚሰራው በመሆኑ በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት የክትትል የማይሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

130. በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የግብር አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት ደግሞ፣

- ✓ በቅ/ጽ/ቤት በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች መረጃውን ወቅታዊ ከማድረግ ባሻገር ተገቢውን የግብር አሰባሰብና ክትትል አፈፃፀም ከግብርና ታክስ አዋጆች ይህንን ለማስፈፀም በወጣው ደንብ እንዲሁም ባለስልጣኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ

ባወጣው መመሪያዎች እና በስራ ሂደቱ ማንዋል መሠረት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ግብርና ታክስ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ የግብር/ታክስ ግዴታቸውን ባልተወጡ ግብር ከፋዮች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 77 እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/94 አንቀጽ 31 ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ግብር እና ታክስ የሚውል መሆኑን፣

- ✓ በቅ/ጽ/ቤቱ የተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች እንዲሁም በስራ ሂደቱ የሚከናወኑ ድርጅቱ በራሱ ፍቃድ ባሳወቀው መሠረት የሚፈለግበት የግብር እና ታክስ እዳዎች በየበጀት ዓመቱ በግብር ከፋዩ፣ በኦዲት ዓይነትና በግብር /ታክስ ዓይነት ተጠናቅሮ መረጃ የሚያዝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

131. ይሁን እንጂ ከ2002-2005 በጀት ዓመታት በሦስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ላይ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ውስጥ ስንቱ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ በኮሚቴው በተሰጠው የውሳኔ ዓይነት እንዲሁም በስራ ሂደቱ የተደረገ ማስተካከያ/የተወሰደ እርምጃ/ መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳተፈ የተተነተነና ተጠናቅሮ የተያዘ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

132. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተቋሙ አደረጃጀት ላይ በግልፅ እንደተመለከተው በኦዲተሮች ተወስኖ የወጣው የውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው ግብር/ታክስ፣ ወለድ እና መቀጫ በአግባቡ መሰብሰቡን እንዲሁም ግብር ከፋይ ድርጅቱ አቤቱታ ማቅረቡን የሚከታተለው የታክስ ኦዲት ክፍል ሳይሆን የዕዳ ክትትል በመሆኑ በተወሰነ መልኩ መዘናጋት የሚታይ መሆኑንና ይህንን ክፍተት ለመድፈን ከታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በየወሩ በሚላከው የሪፖርት ግብረ-መልስ ላይ ይህንን ጉዳይ ተከታትለው እንዲገልፁ ቢደረግም በተወሰኑ ቅ/ጽ/ቤቶች ተፈፃሚነት ሲኖረው አብዛኛዎቹ እየተገበሩት አለመሆኑን፣ ለዚህም ምክንያት ብለው የሚያቀርቡት በአደረጃጀቱ ኦዲት ክፍሉን የማይመለከት እንደሆነ የሚገልፁ ቢሆንም፣ በቀጣይ መረጃዎች በቀላሉ የሚገኙበትን አግባብ ከመረጃ ቴክኖሎጂ ጋር በመነጋገር በሲስተም ሁሉም ክፍሎች የሚከታተሉበትን አግባብ ለመፍጠር የአሰራር ስርዓት መዘርጋት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

133. በመሆኑም በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ላይ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቱ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣

በኮሚቴው በተሰጠው የውሳኔ ዓይነት እንዲሁም በስራ ሂደቱ የተደረገ ማስተካከያ/የተወሰደ እርምጃ/ መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳተፈ የተተነተነና የተጠናቀረ መረጃ የማይያዝ በመሆኑ በእያንዳንዱ ኦዲት እና በግብር ዘመኑ በኦዲት የተገኙ ተጨማሪ የግብርና ታክስ ውሳኔዎች ገቢ መሆናቸውን (ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ) ለማረጋገጥ ካለማስቻሉ በተጨማሪ የእያንዳንዱን ኦዲትና የኦዲት ባለሙያ ውጤታማነት ለመገምገምና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ አላስችልም፡፡

**የግብርናታክስ ቅሬታ አቀራረብና አፈታትን በተመለከተ፣**

134. በኦዲት ውጤት ከግብር ከፋይ ጋር ስምምነት ያልተደረሰባቸው እና ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ የቀረቡ ውሳኔዎች በቢ.ፒ.አር ጥናቱ ላይ በተቀመጠው 5 ቀናት የጊዜ ገደብ ምላሽ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡

135. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጀው የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ የግብርና ታክስ ቅሬታ አቀራረብና አፈታትን በተመለከተ የሚቀርቡ የአቤቱታ ጥያቄዎች በ5 የሥራ ቀናት ውሳኔ እንደሚያገኙ ቢቀመጥም በከፍተኛ ግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤት በተለያየ ወቅት ኦዲት ተደርገው በኦዲት ውሳኔው ላይ ቅሬታ ከገቡ የግብር ከፋይ አቤቱታዎች መካከል በኦዲቱ ወቅት በናሙና በየበጀት ዓመቱ ከተመረጡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ ስለመሰጠቱ በሚጣራበት ወቅት በ2003 ከ53 እስከ 433 ቀናት እና በ2004 ከ50 እስከ 155 ቀናት አቤቱታዎች የሚፈጁ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

136. በተጨማሪም በምዕራብ አዲስ አባባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2003 እስከ 2005 በጀት ዓመታት ለቅሬታ መልስ ለመስጠት የፈጀው ጊዜ በተሰጣቸው የግብርና ታክስ ውሳኔ ላይ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ያቀረቡ ግብር ከፋዮችን ጉዳይ ሲፈተሽ ከታች በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው በአፋጣኝ መልስ/ውሰኔ እንደማይሰጣቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

| አቤቱታው የፈጀው ግዜ | የግ/ከ ብዛት | በመቶኛ | |
|---|---|---|---|
| *በ5 ቀናትውስጥውሳኔያገኙ* | 1 | 0.15% | |
| *ከ6ቀናት እስከ6 ወር* | 413 | 63% | |
| *ከ6 ወርእስከ2 አመት* | 200 | 30.4% | |
| *ከ 2 አመትበላይ* | 36 | 5.5% | |
| *ያልተረጋገጠ* | 8 | 1% | |
| ድምር | 658 | 100.00% | |

137. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በተመለከተ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ በኮሚቴ የተሰየሙ ሲሆን፣ እነዚህ ኃላፊዎች ወይንም ባለሙያዎች ደግሞ በመደበኛ ስራቸው ላይ በተጨማሪነት እንዲያከናውኑ የተመደቡ በመሆኑ በስራ መደራረብና በተለያዩ ምክንያቶች ወቅታዊ ምላሽ ያልተሰጣቸው ቅሬታዎች እንደሚኖሩና ይህንንም ለመቅረፍ ተቋሙ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ መሻሻል እየታየ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

138. በመሆኑም ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የግብር ከፋዮችን እርካታ መፍጠር ካለማስቻሉ በተጨማሪ ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረጉና በባለስልጣን መ/ቤቱም መሰብሰብ ያለበት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ አድርጓል፡፡

**ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ማድረግ በተመለከተ፣**

139. በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እና በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ሊደረግ ይገባል፡፡

140. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ታይተው እንደገና እንዲስተካከሉ ለታክስ ኦዲት ለተመለሱ በ2003 የ25 ድርጅቶች በ2004 በጀት ዓመት የ229 ድርጅቶች እና በ2005 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የ115 ግብር ከፋዮች እንደገና ተወስኖ የወጣው ግብር/ታክስ ብር 1,148,585,429.00፣ ብር 104,263,687.26 እና ብር 175.77 ሚሊዮን እንደ ቅደም ተከተል የተወሰነ መሆኑን፣ ይሁን እንጂ ከአጣሪ ኮሚቴ እንዲስተካከሉ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በምንያህል

ግዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለባቸው የተቀመጠ የጊዜ ስታንዳርድ ካለመኖሩ በተጨማሪ የተደረገውን ማስተካከያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ፣ የግብር ዓይነት፣ በየበጀት ዓመታቱ ተለይተው በቅድመ ኦዲት ከተወሰነው ጋር ማነጻጸር በሚያስችል መልኩ ተጠናቅሮ እንደማይያዝ ተረጋግጧል፡፡

141. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴና በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የኦዲት ውሳኔዎችን አስተካክሎ ለማውጣት ተቀመጠ የጊዜ ስታንደርድ ባይኖርም ለማስተካከል ወደ ታክስ ኦዲት ከተመለሱ ጀምሮ በየቅ/ጽ/ቤቱ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲስተካከሉና ወደ ገቢ እንዲቀየሩ በማድረግ እየተሰራ መሆኑን፣ ነገር ግን የኦዲት ስራው መጀመሪያ የተወሰነውንና ተስተካክሎ የተወሰነውን፣ የተስተካከለበትን ምክንያት ጭምር የሚያሳይ ሪፖርት በኦዲት የስራ ሂደቱ በኩል በአግባቡ እንደማይያዝ የሚታመን መሆኑንና በቀጣይ ከኦዲት በኋላ ወደ ቅሬታ የሚያመሩ ጉዳዮች ምን እንደሆኑና ሊታዩ የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት የታክስ ኦዲት የስራ ሂደቱ ይህንን መከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና መከታተል የሚገባቸው መሆኑን እንደሚረዱ ገልፀዋል፡፡

142. በመሆኑም ከአጣሪ ኮሚቴ እንዲስተካከሉ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በምንያህል ግዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለባቸው የተቀመጠ የጊዜ ስታንዳርድ ባለመኖሩ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ባለመደረጉ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በየደረጃው በአቤቱታ ላይ እንዲቀመጥ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የተደረገውን ማስተካከያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ፣ የግብር ዓይነት በየበጀት ዓመታቱ ተለይተው በቅድመ ኦዲት ከተወሰነው ጋር ማነጻጸር በሚያስችል መልኩ ተጠናቅሮ የማይያዝ በመሆኑ ደግሞ የተደረገው ማስተካከያ በተገቢው መልኩ ስለመከናወኑ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር አላስቻለም፡፡

**በኦዲት ውሳኔ መሰረት የሚገኙ ውዝፍ ዕዳዎችን ማስተዳደርን በተመለከተ፣**

143. የውዝፍ ዕዳውን እድሜ እንዲሁም ሌሎች መረጃዎችን በመጠቀም ሊሰበሰቡ የሚችሉ እና የማይችሉ ዕዳዎችን በመለየት፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ/በተለይ የቅርብ ዕዳዎችን/ ላይ

በማተኮር ሀብትና ንብረት እስከመያዝ የሚደርስ እርምጃ በመውሰድ ውዝፍ የግብር ዕዳ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

144. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች መካከል የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ✓ በ2003 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው ውዝፍ ዕዳ ብር 671.26 ሚሊዮን ውስጥ ብር 615.81 ሚሊዮን በአቤቱታ አጣሪ እና ብር 0.60 ሚሊዮን በግብር ሰሚ ጉባኤ እየታየ ያለ መሆኑን፣
- ✓ በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው ውዝፍ ዕዳ መጠን ብር 1.58 ቢሊዮን ውስጥ ብር 1.43 ቢሊዮን በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ እና ብር 0.81 ሚሊዮን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እየታየ ያለ መሆኑን፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወር መጨረሻ ከነበረው የውዝፍ ዕዳ መጠን ብር 1.59 ቢሊዮን ውስጥ ብር 731.86 ሚሊዮን በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ፣ ብር 0.57 ሚሊዮን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና ብር 422.983 ሚሊዮን በቴክኒክ ኮሚቴ እየታየ ያለና ብር 297.97 ሚሊዮን ደግሞ ወደ ሲዝር የተላለፈ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

  በመሆኑም በየበጀት ዓመቱ ከሚከናወኑ የኦዲት ውሳኔዎች አብዛኛዎቹ ወደ አቤቱታ እንደሚሄዱ እና አፋጣኝ ምላሽ ተሰጥቷቸው ወደ አሰባሰብ በወቅቱ እንዲገቡ የማይደረግ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

145. በተጨማሪም በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከግብር ከፋዮች የሚፈለግ የውዝፍ እዳ መጠን ከ"SIGTAS" በማየት ብቻ ለማወቅ እንዲቻል የግብር ውሳኔዎች፣ የኦዲት ውሳኔዎች፣ ለአቤቱታ አጣሪ /ኮሚቴ/ ግብር ይግባኝ ጉባኤ የቀረቡ አቤቱታዎችና የተደረጉ ማስተካከያዎች እንዲሁም ሌሎች በ"SIGTAS" መመዝገብ ያለባቸው መረጃዎች ለሁሉም ግብር ከፋዮች በአግባቡ የሚመዘገቡ መሆኑን በተመለከተ የቅ/ጽ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በተገቢው ሁኔታ ወደ ሲግታስ ቋት የሚገቡ መረጃዎች እንዳሉ ሁሉ በተለያዩ ምክንያቶች በማንዋል የወጣው የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ወደ ሲግታስ ከገባው (Reasses) ጋር ልዩነት ያለው እንደሆነና ድርድቱ ባሳወቀው መሠረት መረጃዎች አልፎ አልፎ

በትክክል የማይገቡና በ"SIGTAS Data base" ችግር ምክንያት መረጃዎች ከማንዋል (hard copy) ጋር የማይጣጣሙ ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡

146. በመሆኑም በአቤቱታ ላይ ያሉ እንዲሁም ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ባለመደረጉ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በየደረጃው በአቤቱታ ላይ እንዲቀመጥ አድርጓል፡፡

**የኦዲት ጥራትን ከማስጠበቅ አንፃር የሚከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ፣**

147. እያንዳንዱ ኦዲት በሚካሄድበት ጊዜ ከጅምሩ አንስቶ፣ ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አፈፃፀሙ ተቀባይነት ባለው የኦዲት አካሄድ መርህ እና የአሰራር ማንዋሉ መሰረት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይገባል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወኑ የታክስ ኦዲቶችን የጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቶቹ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቶቹ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ ለምን እንዳቀረቡና ለቅሬታው መቅረብ ምክንያት የሆነውና ውሳኔው ለማን እንደተሰጠ በየኦዲቱ እየተተነተነ ወጥነት ባለው መልኩ መረጃ ሊያዝ ይገባል፡፡

148. በስራ ሂደቱ በየበጀት አመታቱ የሚከናወኑ እያንዳንዱ የኦዲት ውሳኔዎች በግብር አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ የታክስ ኦዲት ማንዋሎች እንዲሁም ተቀባይነት ባላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሠረት ጥራታቸውን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን በተመለከተ በየደረጃው የማረጋገጥ ስራ መከናወን እና ወጥነት ያለው የስራ ወረቀት መዘጋጀት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ይህ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን ለማጣራት የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

149. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የኦዲት ጥራትን በተመለከተ የኦዲት ጥራት የማረጋገጥ ተግባር የሚከናወነው በዋናው መ/ቤት የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ሲሆን ይህንን በተመለከተ Quality Assurance Audit Manual በዝግጅት ላይ መሆኑን፣ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ግን ማንኛውም የኦዲት ሥራ ሲከናወን የኦዲት ማንዋሉን፡ የግብር አዋጆችንና ደንቦችን እንዲሁም በተለያየ ጊዜ የወጡ

መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን እና ይኸውም በየደረጃው በቡድንም ሆነ በስራ ሂደቱ እየተረጋገጠ ውሳኔው የሚወጣ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

150. በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ደግሞ ከዓመታዊ ዕቅድ እስከ ዓመታዊ ዕቅድ ክንውን ድረስ ኦዲቱ ጥራቱን ጠብቆ መሰራቱን ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን እና በበቂ ሁኔታም መሰራቱን ለማረጋገጥ በውስጥ ኦዲትና ማኔጅመንት በሚሰየመው አካል/ኮሚቴ የሚታይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

151. ይሁን እንጂ በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- ✓ በ2002 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ ከቀረቡ 1035 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 282 አቤቱታዎች በድምሩ 1317 አቤቱታዎች ውስጥ ውሳኔ ያገኙት 879 ሲሆን ከዚህ ውስጥ መካከል 165ቱ(19 በመቶው) አቤቱታዎች ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/የፀደቀ፣ 33ቱ(4 በመቶው) ለግብር ከፋዩ/የተሻረ እና 681ዱ(77 በመቶው) አቤቱታዎች ደግሞ ለባለሰልጣን መስሪያ ቤቱና ለድርጅቱ በጋራ/እንዲስተካከል የተወሰነ ሲሆን፣ የ438ዎቹ አቤቱታዎች ደግሞ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣
- ✓ በ2003 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ  ውስጥ  ከቀረቡ 723 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 343 አቤቱታዎች በድምሩ 1066 አቤቱታዎች ውስጥ 385ቱ ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል 110ቹ (28 በመቶው) ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/የፀና፤ 57ቱ(15 በመቶው) ለግብር ከፋዮቹ/የተሻረ እና 218ቱ (57 በመቶው) ደግሞ በጋራ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱና ለግብር ከፋዩ/እንዲስተካከል ሲወሰን ቀሪዎቹ 27ቱ አቤቱታዎች ደግሞ በበጀት ዓመቱ በተካሄደው የግብር ከፋች ድልድል መሰረት ወደ ምስራቅና ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ሲዛወሩ 654ቱ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣
- ✓ በ2004 በጀት ዓመት በበጀት ዓመቱ  ከቀረቡ 468 አቤቱታዎችና  ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 487 በድምሩ 955 አቤቱታዎች መካከል 898ቱ አቤቱታዎች ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 258ቱ (29 በመቶው) ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/የፀደቀ፤ 422ቱ (47 በመቶው) በጋራ ለግብር ከፋዮቹና ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ/እንዲስተካከል እና 218ቱ (24 በመቶው) ለግብር ከፋዩ/የተሻረ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 57ቱ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ መደረጉ፣ በአቤቱታ

አጣሪ እጅ ያለው በድርጅት ሲገለፅም 28 ድርጅቶች (ብር 801,364,824.00) ናቸው፡፡

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወር ከቀረቡ 255 አቤቱታዎችና ከባለፈው ዓመት ከዞሩ 291 በድምሩ 546 አቤቱታዎች መካከል 196ቱ አቤቱታዎች ውሳኔ ያገኙ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 122ቱ (62 በመቶው) ለቅ/ጽ/ቤቱ/የፀና፣ 61ዱ (31 በመቶው) ለግብር ከፋዩ/የተሻረ እና 13ቱ (7 በመቶው) ለባለስልጣኑና ግብር ከፋዩ በጋራ/እንዲሻሻል ሲወሰን ቀሪዎቹ 350ዎቹ አቤቱታዎች ለሚቀጥለው ወር እንዲተላለፍ መደረጉ፣ /የአቤቱታው ብዛት በድርጅት ሳይሆን በውሳኔ ማስታወቂያ ቁጥር ነው/ ታውቋል፡፡

152. በተጨማሪም በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በ2005 በጀት ዓመት ቅሬታ ተገብቶባቸው አንዲስተካከሉ ውሳኔ ከተሰጣቸው መካከል በናሙና ከተመረጡት 29 ግብር ከፋዮች ውስጥ የሁለት ግብር ከፋዮች የቀድሞው ውሳኔ በኦዲተሮች ትክክል መሆኑ የተረጋገጠ ፣ የ9 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ጠቅላላ ብር 138,012,716.46 የተሻረ፣ የ12 ግብር ከፋዮች ውሳኔ ደግሞ ከነበረው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ብር 802,293,162.76 ወደ ብር 393,377,402.14 ማለትም በብር 408,915,760.62 ልዩነት ዝቅ እንዲል ተደረጎ የተወሰነ እና የ3 ግብር ከፋዮች ከቀድሞው ውሳኔ በብር 96,799,267.65 በብልጫ እንደተወሰነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

153. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በየቅ/ጽ/ቤቱ የሚከናወኑ የግብርና የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች በህግና ደንብ መሰረት ለመከናወናቸው ክትትል ይደረጋል ብለው የሚያምኑ መሆኑን፣ ይህ ማለት ግን በስራ ሂደቱ ውስጥ ስህተቶች አይኖሩም ማለት እንዳልሆነ፣ ለዚህም ለክትትልና ቁጥጥር ይረዳ ዘንድ የ2005 በጀት ዓመት ተቋማዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ በከፍተኛ አመራሩ ውሳኔ እንዲያገኝ በማቅረብ አመራር እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ የግብር ውሳኔዎች በማን ተፈርመው መውጣት እንዳለባቸው የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና በዚህም መነሻነት የኦዲት ውሳኔዎች ተፈርመው ከመውጣታቸው በፊት በቡድን አስተባባሪዎች እንዲሁም በስራ ሂደቱ ቁጥጥር(Quality Control) የሚደረግበት አግባብ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

154. ነገር ግን የኦዲት ጥራት ማረጋገጥ(Quality Assurance) የሚሰራው በዋናው መ/ቤት ቢሆንም እስካሁን ድረስ እንዳልተከናወነና ለዚህም ዋናው ምክንያት የተቀረፀ

ስታንደርድ ባለመኖሩ መሆኑን፣ በቀጣይ የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ቡድኑ ስራውን በአግባቡ መወጣት እንዲችል የኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ማንዋል በዝግጅት ላይ ስለሆነ ሲጠናቀቅ ቡድኑ በአግባቡ ስራውን ይወጣል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

155. በየበጀት አመታቱ የሚከናወኑ እያንዳንዱ የኦዲት ውሳኔዎች በግብር አዋጆች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎች፤ የታክስ ኦዲት ማንዋሎች እንዲሁም ተቀባይነት ባላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሠረት ጥራታቸውን ጠብቀው ባለመከናወናቸው አብዛኞቹ የኦዲት ውሳኔዎች ወደ አቤቱታ እንዲሄዱና ማስተካከያ እንዲደረግባቸው አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ቅ/ጽ/ቤቶች በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቶቹ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቶቹ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ ለምን እንዳቀረቡና ለቅሬታው መቅረብ ምክንያት የሆነውና ለማን እንደተወሰነ በየኦዲቱ እየተተነተነ ወጥነት ባለው መልኩ መረጃ የማይያዝ በመሆኑ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ምክንያት በማጥናት የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ አላስቻለም፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

156. በሪፖርቱ ክፍል ሁለት ከተዘረዘሩት ችግሮች እና የአሰራር ግድፈቶች በመነሳት በእኛ አስተያየት፤

- ✓ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂውን ሰነዱን መሰረት ያደረጉ የአሰራር ማንዋሎች/መመሪያዎች/ ተዘጋጅተው ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው አለመደረጉ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባር ግልጽነት፣ ተጠያቂነት ያለበት እና ወጥነት ያለው የኦዲት የአሠራር ሥርዓት እንዲከተል የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ የተከናወኑ የታክስ ኦዲቶች በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባር በመከላከል የገቢ ህግ ተገገርነትን በማረጋገጥ ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፍል ያደረገውን አስተዋፅኦ መገምገም የሚያስችል የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በባለስልጣን መ/ቤቱ ህግ ማስከበርን በተመለከተ በስትራቴጂክ ዘመኑ የያዛቸውን ዒላማዎች ከማሳካት ዓንፃር የታክስ ኦዲቱ ያበረከተው ተጨባጭ አስተዋፅኦም/ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት/ፋይዳ መገምገመም የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ በኦዲት ተጨማሪ ገቢ መወሰንን ብቻ እንደ ግብ ማስቀመጥና የውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት መጠቀም አንድ ሰፊና ውስብስብ ስራ ያለው ማህደር ላይ በተደረገ ኦዲት በጣም አነስተኛ ተጨማሪ ገቢ ሊገኝ የሚችል በመሆኑና በሌላ ቀለል ያለና ብዙ ቀናትን ባልፈጀ የኦዲት ፋይል ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ተጨማሪ ገቢ ሊገኝ የሚችል በመሆኑ የኦዲተሮች ዕቅድ አፈፃፀም ሲገመገም ልዩነትን የሚያስከትልና ኦዲተሮችንም ወዳልተፈለገ ውሳኔ እንዲያመሩ የሚያደርግ መሆኑ፣
- ✓ እንደ አንድ ተቋም የተዘጋጀውን ወጥ የሆነ የኦዲት ዕቅድ ጠብቆ በመሥራት በርካታ አላስፈላጊ በሆኑ ምክንያቶች የግብር ከፋዮች እርካታ ለመቀነስ እና በተሰማራው ውስን የሰለጠነ የኦዲት ሙያተኛ ልክ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት የማያስችል መሆኑ፣

- ✓ ኦዲቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲናቀቁ አለመደረጉ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የግብር ከፋዮችን እርካታ መፍጠር ካለማስቻሉ በተጨማሪ በቅ/ፅ/ቤቶች ከሚገኘው ግብር ከፋይ ብዛት አንፃር በቂ የኦዲት ሽፋን ባለመኖሩ በኦዲት ሊገኝ የሚችል ተጨማሪ ገቢ ሳይሰበሰብ የይርጋው ጊዜ ሊያልፍ የሚችልበት ስጋት የሚፈጥር መሆኑ፣
- ✓ ግብር ከፋዩን ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል አካል በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ ባለመቋቋሙ፣ የሚከናወነውን ተግባር/ሂደት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር መመሪያ ባለመዘጋጀቱ፣ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሚገኙ ለሁሉም ግብር ከፋዮች የጠራና የተደራጀ መረጃ(profile) ባለመያዙና የሁሉንም የሚያስተዳድሯቸውን ግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ በግልጽ እንዲታወቅ አለመደረጉ ለኦዲት የተመረጡት ግብር ከፋዮች ግልጽነት ባለው መንገድ ስለመመረጣቸው ለማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑ በተጨማሪ ሥጋትን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ተቋሙ ያለውን ሀብት በተመረጡና ከፍተኛ ፋይዳ ባላቸው ግብር ከፋዮች ላይ የኦዲት ስምሪት በማድረግ የተቋሙን ራዕይ እውን ማድረግ እና በግብር አስገቢው መ/ቤትና ግብር ከፋዩ ኅ/ሰብ መካከል የሚፈጥረው ያለመተማመን ችግርና የሕግ ተገዥነት እንዲሁም በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚያስከትለውን የወጪ ጫና መቀነስ የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወነው ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራትን /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች ለመደልደል የሚያስችል ወጥ የሆነ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የስራውን ውስብስብነት፣ ግብር ከፋዩ የተሰማራበትን ዘርፍ፣ የቡድኑን ወይም የኦዲተሩን እውቀትና ክህሎት ወ.ዘ.ተ መሰረት በማድረግ ብቃት ባላቸው ኦዲተሮች እንዳይከናወንና ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን የመደልደል ወይም የማከፋፈል ስራው ወጥነት ባለው፣ ግልፅ በሆነና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ የተከናወኑት ኦዲቶች የስጋት ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ ቅደም ተከተል የወጣላቸው፣ በወጣው ቅደም ተከተል መሰረትም ኦዲቱ የተከናወነ በተጨማሪም ስራው መች እንደተሰራ፣ በማን እንደተሰራ፣ የት እንደተሰራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ እና ትኩረት የሚሰጣቸው ጭብጦች የተዳሰሱ ስለመሆኑ ለመከታተልና ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ፣

- ✓ ለተከናወኑ ለእያንዳንዱ ኦዲቶች የኦዲት ስራ ወረቀቶች ማህደር ተዘጋጅቶላቸው ባግባቡ ተደራጅተው (ግልፅ እና የተሟሉ) በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችል መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ አለመደረጉ እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበትን አሰራሮች ተከትሎ የተከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የማያስችልና ከተጠያቂነት አንፃር ክፍተት የሚፈጥር መሆኑ፣
- ✓ እያንዳንዱ የስራ ሂደት የኦዲት ስራውን ከመጀመሩ በፊት ወይም የኦዲት ዝግጅቱን አጠናቆ የኦዲት ስምሪቱን ሲጀመር በየኦዲት ፕሮግራሙ መሰረት ኦዲት ተደራጊው ድርጅት ወይም ኩባንያ ስላላቸው መብትና ግዴታ/መቼ ኦዲት እንደሚደረግ፣ ለምን ኦዲት እንደሚደረግና በማን ኦዲት እንደሚደረግ ድርጅቱም ይህንኑ ተገንዝቦ በታክስ ህጉ መሰርት ለኦዲት ስራ የሚያገለግሉ አስፈላጊ ሰነዶችን በወቅቱ እንዲያዘጋጅና ድርሻውን እንዲወጣ በአጠቃላይ ድርጅቱ በኦዲት ሂደት ውስጥ ስላሉት መብትና ግዴታዎች ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው የማይደረግ መሆኑ ኦዲቶች በወቅቱ እንዳይጠናቀቁ እና በኦዲት ተወሰነውም ተጨማሪ ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ የሚያደርግ መሆኑ፣
- ✓ ኦዲተሮች የመጨረሻውን የኦዲት ውሳኔ ከማውጣታቸው በፊት/በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት በእያንዳንዱ የኦዲት ግኝቶች ላይ ከግብር ከፋዩ ጋር ስምምነት እንዲደርሱ ወይም በውሳኔው ላይ ስለመስማማቱ/አለመስማማቱ በግልጽ በሚያሳይ ማስረጃ/በቃለ-ጉባኤ በማስደገፍ ለሁሉም ኦዲቶች እንዲዘጋጅና እንዲያዝ አለመደረጉ ከተከናወኑ ኦዲቶች አብዛኞቹ ወደ አቤቱታ እንዲሄዱ የሚያደርግ በመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱን ለተጨማሪ ጊዜና ወጪ እንደሚዳርጉት መሆኑ፣
- ✓ በታክስ ኦዲት ወቅት ከግብር ከፋይ ከሚቀርብ መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠናቅረው የማይያዙ/የማይሰበሰቡ እና በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ የማይውሉ በመሆኑ በግብር ከፋዩ የሚቀርቡ የታክስ ማስታወቂያዎችና ሌሎች መረጃዎች ትክክለኛነት በግባቡ

ማረጋገጥ የማያስችል መሆኑና መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ መሰብሰብን ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ፣

- ✓ በየበጀት ዓመታቱ የሶስተኛ ወገን መረጃን በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ በማዋል የተገኘ ተጨማሪ ግብር/ገቢ መረጃ ተጠናቅሮ የማይያዝ መሆኑ ተቋሙ የሶስተኛ ወገን መረጃ በመጠቀም የሚያከናውናቸውን የኦዲት እና የአሰስመንት ሥራዎች ውጤታማ ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ላይ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቱ ተማማነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ በኮሚቴው በተሰጠው የውሳኔ ዓይነት እንዲሁም በስራ ሂደቱ የተደረገ ማስተካከያ/የተወሰደ እርምጃ/ መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳተፈ የተተነተነና የተጠናቀረ መረጃ የማይያዝ በመሆኑ በእያንዳንዱ ኦዲት እና በግብር ዘመን በኦዲት የተገኙ ተጨማሪ የግብርና ታክስ ውሳኔዎች ገቢ መሆናቸውን (ተገቢው እርምጃ ስለመወሰዱ) ለማረጋገጥ የማይቻል ከመሆኑ በተጨማሪ የእያንዳንዱን ኦዲትና የኦዲት ባለሙያ ውጤታማነት ለመገምገምና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ አለማስቻሉ፣
- ✓ ቅ/ጽ/ቤቶች በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቱ ተማማነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ ለምን እንዳቀረቡና ለቅሬታው መቅረብ ምክንያት የሆነውና ለማን እንደተወሰነ በየኦዲቱ እየተተነተነ ወጥነት ባለው መልኩ መረጃ የማይያዝ በመሆኑ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ምክንያት በማጥናት የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ የማይቻል መሆኑ፣
- ✓ ከአጣሪ ኮሚቴ እንዲስተካከሉ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በምንያህል ግዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለባቸው የተቀመጠ የጊዜ ስታንዳርድ ባለመኖሩ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተወሰኑ የግብርና የታክስ ውሳኔዎችን በአፋጣኝ አስተካክሎ በማውጣት ወደ አሰባሰብ የአፈጻጸም እንዲገቡ ባለመደረጉ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በየደረጃው በአቤቱታ ላይ እንዲቀመጥ ያደረገ መሆኑ፣
- ✓ የተደረገውን ማስተካከያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ፣ የግብር ዓይነት በየበጀት ዓመታቱ ተለይተው በቅድመ ኦዲት ከተወሰነው ጋር ማነጻጸር በሚያስችል መልኩ ተጠናቅሮ የማይያዝ በመሆኑ ደግሞ የተደረገው ማስተካከያ በተገቢው መልኩ ስለመከናወኑ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የማይቻል መሆኑ፣

ይታመናል፡፡

157. በአጠቃላይ በኦዲቱ እንደተገነዘብነው በባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ ኦዲት ተግባር ግብር ከፋዩ በራሱ እምነት ለታክስ አስተዳደሩ አሳውቆ የከፈለውን ግብርና ታክስ ካለው የታክስ ሕግ አንፃር ከማጣራት ስራ እና ተጨማሪ ገቢ ከመሰብሰብ በዘለለ የታክስ አስተዳደሩን አሰራር እንዲሻሻልና ግብር ከፋዩ በፈቃደኝነት እንዲከፍል ከማስቻል አንፃር ማከናወን እንደሚገባው ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት እና የስጋት ምንጮችን በመለየት፣ ስጋቶችን በመመዘንና ቅደም ተከተል በመስጠት እና ስጋቶችን መሰረት በማድረግ ለግብር ከፋዮች የትምህርትና ምክር አገልግሎት ለመስጠት ስጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት ዕቅድ ይዞ በዕቅዱ መሰረት ኦዲቶችን በማከናወን አፈፃፀማቸውን በየጊዜው የማይገመገም ከሆነ በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባርን በመከላከል የገቢ ህግ ተገዢነትን ለማረጋገጥ የተዘረጋው የአገር ውስጥ ታክስ ኦዲት አሰራር ብቃት ያለውና ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል እያስገነዘብን፤ በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶችን ለማሻሻል፣ በአጠቃላይ የታክስ ኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

158. **የታክስ ህግ ተገዢነትን በማሳደግ ግብር ከፋዩ በፈቃደኝነት የታክስ ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባር/**Tax audit function/ **ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገምን በተመለከተ፤**

- ✓ የታክስ ኦዲት ፖሊሲ እና ስትራቴጂውን ሰነዱን መሰረት ያደረጉ የአሰራር ማንዋሎች/መመሪያዎች/ ባፋጣኝ ተዘጋጅተው ለሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው ሊደረግና ቅ/ጽ/ቤቶችም በመመሪያው መሰረት የታክስ ኦዲት ተግባርን እያከናወኑ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ የተከናወኑ የታክስ ኦዲቶች በግብር ከፋዮች ሊፈጠር የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ግብርና ታክስ የመደበቅና የመሰወር ተግባር በመከላከል የገቢ ህግ ተገዢነትን በማረጋገጥ ግብር ከፋዩ ያለበትን ግብር በፍቃደኝነት እንዲከፍል ያደረገውን አስተዋፅኦ መገምገም የሚያስችል ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚያከናውናቸው ሌሎች የህግ ማስከበር ስራዎች የተናጠል ሊለካ የሚችል የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት በተቋም ደረጃ ተዘጋጅቶ በተቋሙም ሆነ በቅ/ጽ/ቤቶች የኦዲት ዕቅድ ውስጥ ሊካተት ይገባል፡፡
- ✓ የታክስ ኦዲቱ ያበረከተው ተጨባጭ አስተዋፅኦም/ያስገኘው አጠቃላይ ውጤት/ፋይዳ በየደረጃው( በቅ/ጽ/ቤቶችም ሆነ በተቋም) በየዓመቱ መገምገመም ይኖርበታል
- ✓ ቅ/ጽ/ቤቶች እንደ ተቋም የተዘጋጀውን ወጥ የሆነ የኦዲት ዕቅድ መሰርት በማድረግ ስለማቀዳቸው እና ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በዋናው መ/ቤት ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወኑት ኦዲቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እየተናቀቁ ስለመሆኑ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

159. **በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ያለው የታክስ ኦዲት አፈፃፀም ግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና ወጥነት ባለው መልኩ ደረጃውን ጠብቆ ስለመከናወኑ መገምገምን በተመለከተ፤**

- ✓ የግብርና ታክስ ኦዲት ስራዎችን ተገቢና ምቹ በሆነ መልክ ለማደራጀት፣ ለመመደብና ለመገምገም እንዲሁም ግብር ከፋዩን በእኩልነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለታክስ ኦዲት ለመምረጥ የሚያስችል አካል በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ በሆነ መልኩ መቋቋም ይኖርበታል፡፡

- ✓ በተቋቋመው አካል የሚከናወነውን ተግባር/ሂደት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር መመሪያ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- ✓ በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሚገኙ ለሁሉም ግብር ከፋዮች የጠራና የተደራጀ መረጃ (profile) መያዝ ይኖርበታል፡፡
- ✓ በቅ/ጽ/ቤቶች ለሚከናወነው ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራትን /ኦዲት ኬዝ/ ለኦዲተሮች ለመደልደል የሚያስችል የስራውን ውስብስብነት፣ ግብር ከፋዩ የተሰማራበትን ዘርፍ፣ የቡድኑን ወይም የኦዲተሩን እውቀትና ክህሎት ወ.ዘ.ተ ያገናዘበ ወጥ የሆነ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም የተዘጋጀውን መመሪያ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን የመደልደል ወይም የማከፋፈል ስራው ወጥነት ባለው፣ ግልፅ በሆነና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መደልደል ይኖርባቸዋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም የተዘጋጀውን መመሪያ ኦዲት የሚደረጉ ግብር ከፋዮችን የመደልደል ወይም የማከፋፈል ስራው ወጥነት ባለው፣ ግልፅ በሆነና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እያከናወኑ ስለመሆኑ በዋናው መ/ቤት ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ የተከናወኑት ኦዲቶች የስጋት ደረጃቸውን መሰረት አድርጎ ቅደም ተከተል የወጣላቸው፣ በወጣው ቅደም ተከተል መሰረትም ኦዲቱ የተከናወነ በተጨማሪም ስራው መች እንደተሰራ፣ በማን እንደተሰራ፣ የት እንደተሰራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ እና ትኩረት የሚሰጣቸው ጭብጦች የተዳሰሱ ስለመሆኑ ለመከታተልና ለማረጋገጥ በማያስችል መልኩ መረጃዎች ሊደራጁና ተጠናቅረው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ በየቅ/ጽ/ቤቶች ለተከናወኑ ለእያንዳንዱ ኦዲቶች የኦዲት ስራ ወረቀቶች ማህደር ተዘጋጅቶላቸውና ባግባቡ ተደራጅተው (ግልፅ እና የተሟሉ) በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ በሚያስችል መልኩ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ እያንዳንዱ የስራ ሂደት የኦዲት ስራውን ከመጀመሩ በፊት ወይም የኦዲት ዝግጅቱን አጠናቆ የኦዲት ስምሪቱን ሲጀመር በየኦዲት ፕሮግራሙ መሰረት ኦዲት ተደራጊው ድርጅት ወይም ኩባንያ ስላላቸው መብትና ግዴታ/መቼ ኦዲት እንደሚደረግ፣ ለምን ኦዲት እንደሚደረግና በማን ኦዲት እንደሚደረግ ድርጅቱም ይህንኑ ተገንዝቦ በታክስ ህጉ መሰርት ለኦዲት ስራ የሚያገለግሉ አስፈላጊ ሰነዶችን በወቅቱ እንዲያዘጋጅና ድርሻውን እንዲወጣ በአጠቃላይ ድርጅቱ በኦዲት ሂደት ውስጥ ስላሉት መብትና ግዴታዎች ግልጽ


የሆነ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል በማስረጃ የተደገፈ ስልት ተቀርፆ ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

- ✓ ኦዲተሮች የመጨረሻውን የኦዲት ውሳኔ ከማውጣታቸው በፊት/ በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት በእያንዳንዱ የኦዲት ግኝቶች ላይ ከግብር ከፋዩ ጋር ስምምነት እንዲደርሱ ወይም በውሳኔው ላይ ስለመስማማቱ/ አለመስማማቱ በግልጽ በሚያሳይ ማስረጃ/ በቃለ-ጉባኤ በማስደገፍ ለሁሉም ኦዲቶች እንዲዘጋጅና እንዲያዝ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ በታክስ ኦዲት ወቅት ከግብር ከፋይ ከሚቀርብ መረጃ በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት እንዲደረጉ ለተመረጡ ለሁሉም የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲት ስራው የሚያገለግሉ የሶስተኛ ወገን መረጃዎች ኦዲቱ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው ተጠናቅረው ሊያዙ እና በኦዲት ወቅትም በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡
- ✓ በየበጀት ዓመታቱ የሶስተኛ ወገን መረጃን በኦዲት ወቅት ጥቅም ላይ በማዋል የተገኘ ተጨማሪ ግብር/ገቢ መረጃ ተጠናቅሮ መያዝና ተቋሙ የሶስተኛ ወገን መረጃ በመጠቀም የሚያከናውናቸውን የኦዲት እና የአሰስመንት ሥራዎች ውጤታማ ለማረጋገጥ በየወቅቱ መገምገም ይኖርበታል፡፡
- ✓ በተከናወኑ የታክስ ኦዲት ውሳኔዎች ላይ በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቱ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ በኮሚቴው በተሰጠው የውሳኔ ዓይነት እንዲሁም በስራ ሂደቱ የተደረገ ማስተካከያ/የተወሰደ እርምጃ/ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያሳተፈ የተተነተነና የተጠናቀረ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ቅ/ጽ/ቤቶች በየበጀት ዓመታቱ ኦዲት ከተደረጉት ግብር ከፋዮች ስንቱ ተማምነው እንደከፈሉ፣ ስንቱ ቅሬታ እንዳቀረቡ፣ ለምን እንዳቀረቡና ለቅሬታው መቅረብ ምክንያት የሆነውና ለማን እንደተወሰነ በየኦዲቱ እየተተነተነ ወጥነት ባለው መልኩ መረጃ ሊያዝና በተደጋጋሚ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ምክንያት በማጥናት የማሻሻያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ከአጣሪ ኮሚቴ እንዲስተካከሉ የሚወሰኑት ውሳኔዎች በምንያህል ግዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለባቸው የሚወስን የጊዜ ስታንዳርድ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

- ✓ የተደረገውን ማስተካከያ በእያንዳንዱ ግብር ከፋይ፣ የግብር ዓይነት በየበጀት ዓመታቱ ተለይተው በቅድመ ኦዲት ከተወሰነው ጋር ማነጻጸር በሚያስችል መልኩ ተጠናቅሮ ሊያዝና የተደረገው ማስተካከያ በተገቢው መልኩ ስለመከናወኑ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የቀና ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1 ፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 2. በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም ዘጠኝ ወራት የተከናወኑ የኦዲት ስራዎችና የተወሰነ ተጨማሪ ገቢ

| 2004 በጀት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የኦዲት ዓይነት | የግብር ከፋይ ብዛት | ፍሬ ግብር | ወለድ | መቀጫ | ድምር |
| አጠቃላይ ኦዲት | 522 | 401,188,893.67 | 183,241,203.36 | 482,349,237.39 | 1,066,779,334.42 |
| ዴስክ ኦዲት | | | | | 0.00 |
| የካፒታል ዕድገት | 273 | 8,738,400.38 | | | 8,738,400.38 |
| ልዩ ኦዲት | 15 | 106,181,703.08 | | | 106,181,703.08 |
| መደበኛ ውሳኔ | 250 | 192,166.25 | 7,254.14 | 1,023,279.83 | 1,222,700.22 |
| ዲቪደንድ | | | | | 0.00 |
| **ድምር** | **1060** | **516,301,163.38** | **183,248,457.50** | **483,372,517.22** | **1,182,922,138.10** |

| 2005 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የኦዲት ዓይነት | የግብር ከፋይ ብዛት | ፍሬ ግብር | ወለድ | መቀጫ | ድምር |
| አጠቃላይ ኦዲት | 382 | 154,100,000.00 | 81,610,000.00 | 187,500,000.00 | 423,210,000.00 |
| ዴስክ ኦዲት | 26 | 43,420,543.76 | | | 43,420,543.76 |
| የካፒታል ዕድገት | 126 | 4,960,000.00 | | | 4,960,000.00 |
| ልዩ ኦዲት | 23 | 127,010,000.00 | 38,540,000.00 | 127,460,000.00 | 293,010,000.00 |
| መደበኛ ውሳኔ | | | | | - |
| ዲቪደንድ | 2707 | 97,540,000.00 | 54,000,000.00 | 68,650,000.00 | 220,190,000.00 |
| **ድምር** | **3264** | **427,030,543.76** | **174,150,000.00** | **383,610,000.00** | **984,790,543.76** |

# አባሪ 3፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

**ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡-የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን**

**የኦዲት አካባቢ፡- የአገር ውስጥ ግብር/ታክስ ኦዲት ተግባር አፈፃፀም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ**

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ | የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. የታክስ ህግ ተገዢነትን በማሳደግ ግብር ከፋይ በፈቃደኝነት የታክስ ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የታክስ ኦዲት ተግባር/Tax audit function/ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ | 1.1 ባለስልጣኑ የተቋቋመበትን ዓላማዎች መሰረት ያደረገ የታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ አፈጻጸሙም በተቋም ደረጃ በየአመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 1.2 በታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂው ላይ የተቀመጠውን የታክስ ኦዲት መርህ/tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የረዥም፣ መካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ተቋማዊ ዕቅድ ሊዘጋጅና በሁሉም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የዕቅድ አፈጻጸሙም በየወቅቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ በግምገማው ውጤት መሰረትም ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 ባለስልጣኑ ያለውን ውስን ሀብት በተመረጡና ከፍተኛ ፋይዳ ባላቸው ግብር ከፋዮች ላይ የኦዲት ስምሪት ለማድረግ የሚያስችል የግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ መምረጫ መስፈርት በተቋም ደረጃ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.4 በታክስ ኦዲት ፖሊሲና ስትራቴጂው መርህ እና የግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ መሰረት ያደረገ በዘርፍ ላይ ያተኮረ /Sector Specific/ የኦዲት ስራ፣ ተገቢው የኦዲት አይነት እና የኦዲት ሽፋን ዝርዝር ዕቅድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 የግብር ከፋዮች ደረጃን፣ የኦዲት አይነት እንዲሁም የንግዱን እንቅስቃሴ መሰረት ያደረገ የኦዲት የጊዜ ተመን/ ስታንደርድ/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ኦዲትም በተቀመጠው የኦዲት ጊዜ ተመን ውስጥ ስለመከናወኑ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.6 ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራትን /ኦዲት ኬዝ / ግልፅ፣ ተጠያቂነት ባለው እና ወጥ በሆነ መልኩ ለመምረጥ የሚያስችል የግብር ከፋዮች ማህደር መምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ መስፈርቱም በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ስለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡ |
| | 1.7 የኦዲት ስራ አፈፃፀም ደረጃውን የጠበቀና የንግዱን እንቅስቃሴ ተከትሎ ክህሎቱ ባላቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን የሚያስችል ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች የሚመሩበት ወጥ የሆነ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በመስፈርቱ መሰረት ተግባራዊ ስለማድረጋቸው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.8 ከተወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ/ ምደባ እስከ ኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ድረስ ያለውን የስራ ፍሰት ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ስልት ተቀርፆ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.9 በቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወኑ የታክስ ኦዲቶችን የጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.10 የታክስ ኦዲት ስራዎችን ውጤታማነት ለመለካት የሚያስችል የታክስ ኦደት መርህን/ tax audit principles/ መሰረት ያደረገ የኦዲት ውጤታማነት መመዘኛ መስፈርት ሊዘጋጅና እያንዳንዱ የኦዲት ስራ ሊመዘን ይገባል፡፡ |
| | 1.11 በተከናወኑ የኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተገቢው እርምጃም ስለመወሰዱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.12 በዕቅድ የተቀመጡትን የኦዲት ሥራዎች በታቀደው መሰረት እየተፈጸሙ መሆኑ በታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ክትትል ሊደረግና ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.13 የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ከስነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ጋር በመቀናጀት በታክስ ኦዲት ዙሪያ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ለማስተካከል የሚያስችሉ ዘዴዎች እና ስልቶች ተቀርፀው |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/ | የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| | ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| 2. በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ያለው የታክስ ኦዲት አፈፃፀም ግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና ወጥነት ባለው መልኩ ደረጃውን ጠብቆ ስለመከናወኑ መገምገም፤ | 2.1 በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀውን ተቋማዊ የኦዲት ስራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ዝርዝር የኦዲት ዕቅድ ሊያዘጋጁና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በተቋም ደረጃ በተዘጋጀው የግብር ከፋዮች የስጋት ደረጃ መምረጫ መስፈርት መሰረት የግብር ከፋይ ማህደራትን ሊመርጡና ተገቢውን የኦዲት አይነት ሊያከናውኑ ይገባል፡፡ |
| | 2.3 ኦዲት እንዲደረጉ የሚወሰኑ ማህደራት /ኦዲት ኬዝ / ለኦዲተሮች ለመምራት በተዘጋጀው ወጥ የሆነ መስፈርት መሰረት የግብር ከፋይ ማህደራት ለኦዲተሮች ሊመሩ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 ለኦዲት የተመሩ የግብር ከፋይ ማህደራት/ፋይሎች/ ኦዲት በተቀመጠው የጊዜ ዕቅድ እና በጥራት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ |
| | 2.5 በተከናወኑ የኦዲት ውጤቶች መሰረት ተገቢው ዕርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተገቢው እርምጃም ስለመወሰዱ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 2.6 የታክስ ኦዲት ከመከናወኑ በፊት፣ በኦዲቱ ወቅት እና ከኦዲቱ በኃላ ግብር ከፋዮች ስላላቸው መብትና ግዴታ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.7 በኦዲት ወቅት የግብር ውሳኔ ለማዘጋጀት የታክስ ኦዲተሮች አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን በትክክል በመተርጎም ግብር ሊወስኑ ይገባል፡፡ |
| | 2.8 ኦዲተሮች የታክስ ህጎችን ወጥ በሆነ መልኩ እየተገበሩ ስለመሆናቸው በስራ ሂደቱ ኃላፊ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.9 በታክስ ኦዲት ወቅት የሶስተኛ ወገን ፣ የዊዝሆልዲንግ እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚገኙ መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ መረጃዎቹም ባግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.10 ከግብር ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ በመቀነስ በተቻለ መጠን በልዩነት በሚወሰነው ግብር/ታክስ ላይ በመተማመን ያለ አቤቱታ የሚከፈልበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በኦዲት ማጠቃለያ ወቅት የመውጫ ስብሰባ በማዘጋጀት በኦዲት ውጤት ላይ ውይይት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.11 በኦዲት ውጤት ከግብር ከፋይ ጋር ስምምነት ያልተደረሰባቸው እና ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ የቀረቡ ውሳኔዎች በቢ.ፒ.አር ጥናቱ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ምላሽ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.12 የቅ/ጽ/ቤቱ የኦዲት የስራ ሂደት ከሰው ሀብት ልማት ጋር በመቀናጀት በቅ/ጽ/ቤቱ ስር የሚገኙ የኦዲት ባለሙያዎችን የአቅም ውስንነት በመለየት ተገቢውን ስልጠና በወቅቱ እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.13 እያንዳንዱ ኦዲት በሚካሄድበት ጊዜ ከጅምሩ አንስቶ ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አፈፃፀሙ ተቀባይነት ባለው የኦዲት አካሄድ መርህ እና የአሰራር ማንዋሉ መሰረት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 2.14 እያንዳንዱ ኦዲት ሲካሄድ መከተል ያለበት አሰራሮች በኦዲት ስራ ወረቀቶች የተደገፉ እንዲሁም በኦዲተሮች የተዘጋጁት መግለጫዎችና ሌሎች ሰነዶች ተፈርመው ከኦዲት ውጤቱ ማጠቃለያ ጋር ለስራ ሂደቱ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 2.15 የስራ ሂደቱ የኦዲት ስራው በተሟላ፣ ተጠያቂነት ባለውና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የተከናወነ መሆኑን የአፈፃፀም ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 2.16 የኦዲት ስራ ወረቀቶች ባግባቡ ሊደራጁ (ግልፅ እና የተሟሉ) እና በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ እንዲችሉ በህግ ለተወሰነው የጊዜ ገደብ በአግባቡ ሊጠበቁ በሚችሉበት ቦታ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ |
| | 2.17 በቅ/ጽ/ቤቱ በታክስ ኦዲተሮች የተወሰነውን እና የተሰበሰበውን የግብር/ታክስ መጠን እንዲሁም ቅሬታ የቀረበበትን እና የተሰጠውን ውሳኔ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 2.18 ምርጥ የኦዲት ግኝቶች እየተለዩ ለመማማሪያነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ |